# ዝሁ

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት

የዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት ግብና ዓላማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ይዘት ያላቸውን ቅዱሳንን የሚመግቡና ከስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች የሚያስጠነቅቁ ከአጫጭር መጣጥፎች እስከ ትልልቅ የማስተማሪያ መርጃዎች በማዘጋጀት ቤተ ክርስቲያንን መደገፍና በዚህም እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

ቁጥር ፴፫
ሚያዝያ ፪ሺ፰ ፰ ዓመተ ምሕረት
APRIL 2016


ብዙ ሰላም ይህን ለምታነብቡ ሁሉ ይሁን።

በዚህ ስርጭት አንድ መጣጥፍ ብቻ ነው ያቀረብኩት።

<u>የ'ሐዋርያዎቻችን' ኢየሱስ፤</u> የኢየሱስ ማንነት ከክርስትና ውጪም ከውስጥም ጥቃት ሲደርስበት ኖሯል። በዚህ ዝግጅት ሐዋርያ ዘላለም (ፖዝ) ጌታቸው ተከስተ የሚያሳየንን እስከ መሰይጠን (ሰይጣን መሆን) የደረሰና ለ33 ዓመታት ሰው ብቻ እንጂ ፈጽሞ አምላክነት ስላልነበረው ኢየሱስ እንዲሁም ሌሎች ትምህርቶቹን እናያለን።

በዚህ ስርጭት ተከታታይ የሆኑትን ስለ እስላምና ክርስትና በንጽጽር መጽሐፍ ሕያሴ እና የፊልጵስዩስ መልእክት ጥናት አልላክሁም፤ ጌታ ቢፈቅድና ብንኖር በሚቀጥለው ስርጭት ይላካሉ።

እነዚህንም ሆነ ማናቸውንም በዕዝራ ላይ የምጽፋቸውን ጽሑፎች ባለቤትነቱን ሳትወስዱ በነፃ ማባዛትም ሆነ ማደል ትችላላችሁ። ባለቤትነቱን ሳትወስዱ ያልኩት ለጽሑፎቹ ተጠያቂና ተወቃሽ እንዳትሆኑ ነው። በነፃ ያልኩትም ለሽያጭ እንዳይቀርብ ነው።

ጌታ ጸጋውን ሰላሙንም ያብዛላችሁ።


ዘላለም መንግሥቱ / ዕዝራ ስነ ጽሑፍ

ezralit@gmail.com




# የዘመናችን 'ሐዋርያዎች' ኢየሱስ

## 'ሐዋርያ' ፖዝ እና የሚሰብከው ኢየሱስ




## መግቢያ

በApril 2016 መጀመሪያ አንድ ማታ ከጥቂት ወንድሞች ጋር ሆነን በExodus TV Show (ቤተልሔም ታፈሰ) የተዘጋጀ የሐዋርያ ዘላለም (ፓዝ) ጌታቸው ተከስተን (ከዚህ በኋላ ሐዋርያ ፖዝ ወይም ፖዝ) ቃለ መጠይቅ ተመለከትን። ይህን ካየሁ በኋላ ተቀምጬ አስተያየታዊ ምላሽ ብቻ እንጂ ጥልቅ ምርመራ ያልተደረገበት የምካቴ እምነት ሥራ ያልሆነ አጭር መጣጥፍ መጻፍ ጀመርኩ። አጭሯን የሦስት ገጽ ሥራ ከጨረስኩ በኋላ ነው ጉዳዩ አሳሳቢ መሆኑን በመገንዘብ በመጠኑ ሰፋ ያደረግሁት። በቃለ መጠይቁ ውስጥ ተጠያቂው ገሃድ ያደረጋቸው ጉልህ የስሕተት ትምህርቶች በቀላሉ መታየት የሌለባቸው መሆናቸውን ራሳቸው የሚገልጡ ናቸው። ይህ በመሆኑም ወደፊት ሌሎችም ሊመልሱት የተገባ ነው።

ጋዜጠኛዋ ከዚያ ያለፉ ገታሪና ተገዳዳሪ ጥያቄዎች እንድታቀርብ ብጠብቅም ከመሰናዶዋና ምናልባት ከአቅሟ አንጻር ማለፊያ ሥራ መሥራቷን አደንቃለሁ። አንድዳንዶቹ ጥያቄዎች ያላሰበችባቸውና ምናልባት ያልተዘጋጀችባቸው በመሆናቸው የተጠያቂውን መልሶች በአጻፋ መመከት እስከማትችል አክብደውባታል። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ኃይለኛ ጥያቄ ተኩሳ ባሩድ አሽትቶ ሌላኛው እስኪተኩስ አድፍጣ የምትጠብቅ ትመስላለች። የማንነት መገኛ የሆኑትን የመጀመሪያ የሕይወት ታሪኮች እና ዳራ ጨርሶ አልነካችም። ከስነ ልቡናዊ ዝግጅት ባለፈ በቂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ስነ መለኮታዊ ዝግጅት አድርጋለች፤ ግን ተጠያቂው ከዐውድ የወጡ ጥቅሶችን እንደ ዶቃ ሲደረድር ወደ መስመር የሚያስገባ ከዝግጅቷም ያለፈ ዝግጅት መኖር ነበረበት። እንዲያም ሆኖ፥ መልካም ጅማሬና የተረጋጋ አረማመድ ነው ብዬ ማበረታታት እፈልጋለሁ። ምናልባት ጋዜጠኛዋ አወያይ (moderator) ሆና አንጻራዊ ጥያቄና ምላሽ ላይ ተሳታፊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስነ መለኮት ላይ የቆመ ሰው አብራ ብታቀርብ መልካም ነበር። መጨረሻ ላይ ተስፋ ሰጥታለችና ይህ ወደፊት ይደረጋል። በጠቅላላው ድንቅ የቃለ ምልልስ ዝግጅት ነው።

ከዝግጅቱ ጋር በተያያዥነት ለመጨመር፥ ጽሑፉን ከጨረስኩ በኋላ በExodus TV Show ያልተካተተ ክፍል ስላለ ያንን እንድመለከት ተነገረኝና ከተጠያቂው በኩል የተለጠፈውን ሁለት ቀዳሚ ክፍሎች አግኝቼ ተመለከትኳቸው። ሁለቱ ክፍሎች ጉልህ የሆኑ ልምምዳዊ አሳቦችን እንጂ ብዙም አስተምህሮታዊ ይዘት ስለሌላቸው፥ እንዲሁም በኢየሱስ ማንነት ላይ በተነገሩት ነገሮች ላይ ለውጥ የማይፈጥሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። በእርግጥም የExodus TV Show የጀመረው ከ3ኛው በመሆኑ ከፊት የተቆረጠ ክፍል እንደነበረው በግልጽ ይታያል። ይህ የቪድዮ ዝግጅቱን በተመለከተ ነው።

በሰዎች ትምህርቶች ላይ ስጽፍ ልማዴ እንደመሆኑ የማደርገው ጽሑፉ ሳይታተምና ሳይበተን ለሚመለከተው ሰው መላክ ነው። ይህንን ጽሑፍም በሐዋርያ ፖዝ አገልግሎት ድረ ገጽ ላይ በሚገኘው የኢሜይል የመገናኛ አድራሻ እንዲሁም በሌላ ሊወክለው በሚችል አንድ ሰው በኩል April 10 ልኬአለሁ። ይህንን ለሚመለከታቸው የመላክ ተግባር የማደርገው ለአስተያየትና ለምላሽ ነው። ይህ የግል አሳብን ለመግለጥ ዕድል ለመክፈት እና የተጻፈው፥ የተነገረው፥ ወይም የተሰጠው ትምህርት እዚህ እንደቀረበው መሆን አለመሆኑ አይተው እንዲነቅሱ ወይም ምላሽ እንዲሰጡ ለማበረታታት ነው። ከፖዝም ከሌላው ሰውም እስካሁን ምላሽ አላገኘሁም።

በዚህ ጽሑፍ የማቀርበው ባገጠጡት ስሕተቶች፥ በተለይም አስተምህሮታዊ በሆኑቱና በኢየሱስ ማንነት ላይ በተቃጡቱ ላይ ብቻ ነው።[1] ብዙ ጊዜ በስህተት ትምህርቶች ወይም በስሕተት አስተማሪዎች ላይ ስጽፍ የምጠይቃቸው ሦስት ጥያቄዎች አሉ። በነዚህ ጥያቄዎች ላይ የማገኘው መልስ 'አዎን' ሆኖ የሚያስጽፍ ነገር ከኖረ ብቻ ነው የምጽፈው። እነዚህ ጥያቄዎች፥

1. ይህ ትምህርት ወይም ይህ ጉዳይ ከቅዱስ ቃሉ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይጻረራል?

2. ጌታ ክርስቶስን ከክብሩ ያወርደዋል?

3. ይህ እንድጽፍበት ያደረገኝ ትምህርት የቅዱሳንን እምነት ያፈርሳል?

በዚህ መጣጥፍ ፖዝ ስለ ኢየሱስ የተናገራቸው ስሕተቶች ወይም የስሕተት ትምህርቶች ከላይ ያልኳቸውን ሦስት መስፈርቶች በትክክል ያሟላሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይጻረራሉ፤ ክርስቶስን ያዋርዳሉ፤ የቅዱሣንን እምነት ያፈርሳሉ። ስለዚህ ነው የምጽፈው።

በቃለ መጠይቁ ውስጥ ይህ ሰው ኢየሱስን አራት ነገሮች አድርጎ አሳይቶአል። እነዚህ አራት ነገሮች፥

1. ፖዝ አድራጊ/አስደራጊ (ፖዝ አስደራጊው ኢየሱስ)፤

2. የሰየጠነው/ሰይጣን የሆነው (ሰይጣኑ ኢየሱስ)፤

---

[1] የቪድዮ ቃለ መጠይቁን ከዚህ ምንጭ ማየት ይቻላል፤ https://www.youtube.com/watch?v=vXh_XvSeR8o። በአራት መሰናዶዎች የተሰራጨ ሲሆን ቀጣዮቹን ክፍሎች ክፍል አንድ ሲከፈት ያገኙታል። ያልተካተቱትን ሁለት ክፍሎች ደግሞ ከ https://www.youtube.com/watch?v=r2RZ2A2nBSQ ላይ በመሄድ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች ያገኙታል።



ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

3. ሰው ብቻ/ሰው ብቻው (ሰውየው ኢየሱስ)፤

4. ታጃቢ (ታጃቢው ኢየሱስ)።

በቃለ መጠይቁ ውስጥ ብዙ ዝባዝንኬ የሆኑ ልምምዳዊ ጉዳዮች ቢነሡም የሚያስጽፉኝ ጉዳዮች ላይ ያነሳኋቸውን መስፈርት የማያሟሉ በመሆናቸው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በነዚህ አራት ነጥቦች ላይ ብቻ አተኩራለሁ። አራተኛውና የመጨረሻው ርእስ የታይታ ጥማትን አመላካች እንጂ አስተምህሮታዊ ጥንካሬ ወይም ጥቅምና ጉዳት የለውምና ልተወው ነበር። ሆኖም ግን ኢየሱስ በምሳሌነትና በሞዴልነት የተነገረበት ስሕተት ስለሆነ በመጨረሻ ላነሣው ሆኗል። ሌሎቹ ሦስቱ ነጥቦችም ቢሆኑ ቃለ መጠይቁን በሚመጥን በመጠነኛ ጥልቀት እንጂ እጅግ ጠልቄ አልጻፍኩበትም። ይህን ስል በራሱ ትምህርት ላይ ብቻ ምላሽ ለመስጠት ያህል ጻፍኩ እንጂ፥ ለምሳሌ ከእርሱ በፊት ስለነዚህ ስሕተቶች የተናገሩትን እና የጻፉትን ሰዎች ከማመልከት ብዙም ያለፈ አላደረግሁም። ለምሳሌ፥ ኢየሱስ ሰየጠነ የሚሉ እና ኢየሱስ ሰው ብቻ ነበረ የሚሉ ሌሎች ከፖዝ በፊት ኖረው ያውቃሉ። እነዚህን እዚህ ጽሑፍ ውስጥ በምልከታ ደረጃ ብቻ ነው በመጠኑ ያነሣሁት። ትኩረቴ ራሱ ፖዝ የተናገረው እና የቃሉ ምላሽ ነው።

እንደ መግቢያ ግን አንድ ጥያቄ መጣልና ከዚያ መንደርደር እሻለሁ። ያም፥ 'እነዚህ እንደ ፖዝ ያሉት ሰዎች የሚናገሩት ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ነው ወይስ እነርሱ የፈጠሩት ኢየሱስ?' ብሎ መጠየቅ ተገቢና የመልሳችን መዝገብ ወደሚገኝበት ወደ ቃሉ እንድንሄድ የሚያደርገን ጥያቄ ነው። ዛሬ የምንሰማው ሐሰተኞች አስተማሪዎች የሚሰብኩን ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ሳይሆን በምናባቸው የፈጠሩት ወይም ሰይጣን ፈጥሮ ያቀበላቸው ሌላ ኢየሱስ ነው። በዚህ ሰው ትምህርቶች ውስጥ የምናገኘው ኢየሱስ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ቆሮ. 11፥4 *የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።* ያለው ያኔም አሁንም እውነት ነው። ሌላ ኢየሱስ፥ ልዩ መንፈስ፥ ልዩ ወንጌል። ይህ ታዲያ የሚታገሡት ትምህርት መሆን የለበትም።

# 1. ፖዝ አስደራጊው ኢየሱስ?

ፖዝ ከሚለው ቃል ልጀምር። ሐዋርያ ዘላለም የቅጽል ስሙ ፖዝ (pause) መሆኑን ይናገራል። Pause የእንግሊዝኛ ቃል ነው። ቋንቋ በዘመናት የሚወለድና እየኖረ የሚያድግ ኖሮም ሊሞት የሚችል የመግባቢያ መሣሪያ ነው። አማርኛ ከግዕዝ አብራክ እንደወጣ፥ እንግሊዝኛ ላቲንንም (ሮማይስጥን) ጨምሮ ከተለያዩ ቋንቋዎች አብራክ የወጣ ነው። Pause ከሮማይስጥ የተወሰደ የእንግሊዝኛ ቃል ነው። አንድን ነገር ለዘለቄታው ሳይሆን ለጊዜው ማቆም ማለት ነው። ልክ በሙዚቃ ወይም መዝሙር ማጫወቻ መዝሙር ሲዘመር ቆይቶ ለጊዜው አቁሞ ኋላ እንዲቀጥል እንደሚደረገው ማለት ነው። ወይም አንድ መኪና ኬላ ላይ ቆም ብሎ ተፈትሾ ጉዞውን እንዲቀጥል ሲደረግ ማለት ነው። ሐዋርያ ፖዝ ስሙ ለምን ፖዝ እንደተባለ በቃለ መጠይቁ ሲናገር፥

> እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የድህነትን፥ የኃጢአትን፥ የሞትን፥ የበሽታን አካሄድ ፖዝ አርጓል፤ አቁሟቸዋል። እነዚህ ነገሮች በሰው ሕይወት ውስጥ ፍሰታቸው ተከልክሏል። እኛ ግን እሱን ፓርት አናይም። የቆሙት በመስቀል ነው። ልክ ይኼ የቆሙትን ነገሮች ከዚህ ትውልድ ላይ ታቆምልኛለህ፤ አሁን በማስተምርሽ ትምህርት፥ በሚገባሽ እውቀት፥ ይህንን የጨለማ ፍሰት፥ ታቆምልኛለህ አለኝ ማለት ነው። . . . ፖዝ ታረግልኛለህ ሲል ሰዎች እውነትን እንዲያውቁ ታደርጋለህ፤ ባይ ዘ ዌይ፥ ፖዝ ማለት የቃሉ ፍቺ፥ ማቆም ማለት ነው። . . . ፖዝ ማለት ፍቺውን ልንገርሽ፤ ፖዝ ማለት ጳውሎስ ማለት ነው። ሌላ ፍቺ የለውም። ጌታ ያለኝ በቀጥታ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? በዚህ ትውልድ መሐል ለኔ ጳውሎስ ነህ ነው ያለኝ። እኔ ጳውሎስ የሚለውን ቃል ትርጉሙን ወሰድኩኝና ጳውሎስ የሚለው ፊደል የግሪክ ቃል ላይ ሄጄ ሳጠናው የመጀመሪያው ላይ እመጀመሪያው ወርድ ማለት ነው፤ ሊትል ማለት ነው፤ ሩት ኦሪጂናል ኤግዞስቲቭ ኮንኮርዳንስ ሚባል አለ ግሪክና ሂብሩ ያለው፤ ሩት ወርዱ ላይ ሄጄ ስመለከተው ሩት ወርዱ ምን ይላል? ፖዝ ይላል። ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ጳውሎስ የተባለው የትጋ እንደሆነ ታውቂያለሽ? ምን አርጎ ጳውሎስ እንደተባለ ታውቂያለሽ? [ሐዋ. 13፥8-11 ከተነበበ በኋላ] . . . እስከ ጊዜው ፀሐይን አታይም አለው። በሌላ አማርኛ ሰውየውን ምን አረገው? ፖዝ አረገው። ጳውሎስ ፖዝ ነው። ጳውሎስ ማለት ፖዝ ማለት ነው።"

ይህች ናት ትርጎማ! ከስሙ ትርጉም ብንነሣ ለማለት እንጂ ልናገር የምወደው በኢየሱስ ማንነት ላይ ነው። ግን ስሙ ፖዝ ከፖዝ አስደራጊው ጋርም ስለሚገናኝና 'ፖዝ ታረግልኛለህ' ባዩ ኢየሱስ ስለሆነ ነው የማነሣው እንጂ እንዲህ ያለ የፌዝ፥ የቀለለና ወራዳ አተረጓጎም ሊጻፍበትም የተገባው እንኳ አልነበረም። ይህ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችንም ያላሉትን እንዲል እያደረገ ሲፈታ የሚሞክረው በዚህ መንገድ መሆኑን ዝቅ ስንል እናየዋለን።

ጳውሎስ Παῦλος የግሪክ ሳይሆን የሮማይስጥ ቃል ነው። ስም ሳይሆንም ቅጽል ነው፤ እንዳለውም ትርጉሙ ትንሽ፥ ታናሽ ማለት ነው። ከቃል በታች ያሉ ንውሳን የቃል ቁርጥራጮችን ከፈለግን ፖዝንም ጨምሮ ሌላ ሌላ ትርጉምም ልናገኝ እንችላለን። ግስ እንደ ቃል መሠረት ስለሚታይ፥ ስም ወይም ቅጽል በተጻፈባቸው ስፍራዎች ትርጉም ፍለጋ ከግስ ጋር እንዲገናኝ ይገደዳል። 'ይህ፥ ትንሽ የሚባለው ቅጽል ከምን ግስ ጋር ይቀራረባል?' የሚለው ጥያቄ ለቅጽበት ወይም ለትንሽ ጊዜ ማቆም (παύω ፓዎ) ከሚለው ጋር ያቆራኘዋል። ይህ እንግዲህ ቅጽሉን (ትንሽ የሚለውን) ከግስ ጋር ለማቆራኘት የተሄደ አፈታት ነው እንጂ የጳውሎስ ጳውሎስነት ከቅጽበት ጋር የሚገናኝ ስለሆነ አይደለም።

ጳውሎስ የሚለው የጳውሎስ ስም በዚያ ስፍራ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቀሰ እንጂ ሳውል ጳውሎስ የተባለው ቀድሞም ነበረ። *ጳውሎስ የተባለው ሳውል* ግን የሚለው ሐረግ የሚነግረን ስሙ ቀድሞውኑ ጳውሎስ መሆኑን እንጂ ሰዎች ተሰብስበው የዳቦ ስም ሲያወጡለት አይደለም። የፌዝ አተረጓጎም ያልኩት ስለዚህ ነው። እዚያ ድረስ ሳይኬድ ግን ጳውሎስ ለቅጽበት ወይም ለጊዜው ወይም ለትንሽ ጊዜ ማቆም ማለት ሳይሆን፥ ከዚያም ጋር የሚገናኝ ሳይሆን እንዲያው ትንሽ ማለት ብቻ ነው።

'ጳውሎስ ማለት ፖዝ ነው፤ ወይም ለጊዜው ማቆም ነው' ከተባለማ፥ 'ምስጉን ማለት መሰገ ከሚለው ግስ ስለወጣ መመሰግ ማለት ነዋ!' እንደማለት ነው። ግን ነው? አይደለም። የፖል እና ፖዝ ግንኙነት ልክ እንደዚያ ነው ለማለት ይቻላል። ጳውሎስ ከዚያ በፊት ሳውል እንደነበረ እናውቃለን እንጂ ለምን ጳውሎስ እንደተባለ አልተጻፈልንም። ሳውል (שָׁאוּל ሻኡውል) የዕብራይስጥ ቃል ሆኖ መጠየቅ፥ የራስ ማድረግ፥ የኔ ነው፥ ይገባኛል፥ መብቴ ነው ማለት ነው። የጳውሎስ የሮማይስጥ ስም እና የግሪክ አጻጻፍ ሳውሎስ እና ጳውሎስ (Σαῦλος እና Παῦλος) እንደ ግጥም ቤት የሚመታ አጠራር ነው። ምናልባት ጳውሎስ ከአጠራሩ መመሳሰል ጋር አብሮ ከመብተኝነት ይልቅ ትንሽነትንና ትሕትናን የሚያመለክት ስም መምረጡ የማንነት መታወቂያ ቅየራ ይመስላል እንጂ የነገሮች ኬላ ወይም አስቆሚ የመሆኑ ገላጭ አይደለም።

ይህን ስላደረገ (የጠንቋዩ በርያሱስ ወይም ኤልማስ እስከ ጊዜው ዕውር ስለሆነ) ፖዝ ተባለ ካልንማ ጳውሎስ ሺህ ነገር ስላደረገ ሺህ ስም ሊኖረው ነዋ! ደህና፤ ይህ በርያሱስ ዕውር የሆነበት 'እስከጊዜው' የተባለው ቃልስ ፖዝ ከሚለው ቃል ጋር ይዛመድ እንደሆነ ብለን



ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥
የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

ብንመረምር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸውም እናያለን። እስከ ጊዜው ማለት ፖዝ ማድረግ ከሆነ፥ እስከጊዜው ἄχρι καιροῦ አክሪ ካይሩ እና ለጊዜው ማስቆም παύω ፓዎ መመሳሰል ነበረባቸው፤ ግን እንኳን ሊመሳሰሉ ተያይተውም የማያውቁ ምንም ግንኙነት የሌላቸው ሆድና ጀርባ ናቸው። ግሪኩን ትተን ከላይ የጻፍኩትን አማርኛ ብቻ የሚያነብብም ያስተውለዋል።

ፖዝ የፌዝ ብቻ ሳይሆን የተምታቱ፥ የተዘባረቁና የተደናገሩ አፈታቶችን በማቅረብ እየተካነ መጥቶአል። ይህን በመጀመሪያ ያስተዋልኩት፥ *ዝብርቅርቁ ዓለም* በተባለች መጽሐፊት ነው። የመጽሐፊቷ ይዘት እንደ ርእሱ ዝብርቅርቅ ነው። ከዚያ በኋላ ተሻሽሎ ታትሞ እንደሆነ አላውቅም እንጂ የመጀመሪያው እትም እራስና እግሩን ለመለየት የሚያስቸግር ከአማኑኤል ሆስፒታል ማተሚያ ቤት የወጣ የሚመስል መጽሐፍ መሆኑን ያነበቡ ሊታዘቡት ይችላሉ። እዚህ የሚታየውም ከዚያ የባሰ የተደናገረና የሚያደናግር አፈታት ነው። ሌላው በዚህ ሰው አነባበብ እና አፈታት ውስጥ የሚታየው ጥቅሶችን በሚጠቅስበት ጊዜ የሚፈልገውን ስለሚሉ ብቻ እንጂ ዐውድ የሚባል ነገር ስለመኖሩም ግድ የሚሰኝ አይመስልም። ምንም የመጽሐፍ ቅዱስና የስነ መለኮት ትምህርት ዳራ ከሌለው ሰው ስለ ዐውድና ዳራ መጠበቅም አይቻልም።

በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይም ያስተዋልኩት ይህንን ዐውድ-ዘለልነት ነው። ጥቅስን ከስፍራው ፈንቅሎ ከጥቅሱ ውስጥ ቃልን ብቻ ወስዶ መፍታት የስሕተት ትምህርቶች ዋና መታወቂያ ነው። ዋና መታወቂያ። የፖዝ ፍቺ የዚህ ጉልህ ምስክር ነው። ጳውሎስ ማለት ፖዝ ነው፤ ፖዝ ማለት እኔ ነኝ፤ በሽታ፥ ድህነት፥ ሞት፥ ኃጢአት ፖዝ ተደርገዋል ማለት ከፌዝ ያለፈ ጎጂ አፈታት ነው። ይህ ከዐውድ ውስጥ ጥቅስን ፈንቅሎ፥ ከጥቅስ ውስጥ ደግሞ ቃልን ነቅሎ አውጥቶ ማውለብለብ ቃሉን ለማያጠኑ ሰዎች ዕጹብ ድንቅ አፈታት መስሎ ሊታይ ይችላል። ግን የስሕተት አስተማሪዎች ባንዲራ ነው። እንድንጠነቀቅ የሚያደርገን ማስጠንቀቂያም ነው።

ጳውሎስ ማለት ፖዝ ማለት ነው፤ እኔ ጳውሎስ ነኝ፤ ስለዚህ እኔ ፖዝ አድራጊ ነኝ ማለት ከአፈታትና አገነዛዘብ ደንብ የተፋለሰ ብቻ ሳይሆን ብልሹ አፈታት ነው። ይህ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውስጥ አለማለፉን በግልጥ እየተናገረ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች እየከፈተ የሚያስተምር መሆኑ እንዲህ ያሉ ብልሹና ጠማማ ፍቺዎችና አጣማሚ ፈቺዎች እየተባዙ የመምጣታቸውን መንገድ ቀያሽ መሆኑንም የሚያሳይ ነው። ዕውራን መሪዎችን የሚያስለጥኑ ዕውራን አሰልጣኞች ማለት ይህ ነው። በእውነቱ በጸሎትም በትምህርትም ፖዝ መደረግ ያለበት ይህኛው ብልሹ አካሄድ ነው።

ፖዝ ማድረግ ማቆም ከሆነ፥ ኢየሱስ እነዚያን አምስት ነገሮች (ድኅነትን፥ ኃጢአትን፥ ሞትን፥ በሽታን፥ ጨለማን) አቁምልኝ ብሎታል ማለት ነው። Pause ማድረግ ከላይ እንዳልኩት ለዘለቄታ ሳይሆን ለጊዜው ማቆም፥ ወይም ቆም ማድረግ ነው። ኬላ ወይም የመንገድ መብራት ላይ ተሽከርካሪዎች ለትንሽ ጊዜ ቆም ብለው እንደሚቀጥሉት፥ እንደሚሄዱት እነዚህ ነገሮች አንድ ቀን እንደሚቀጥሉ ሆነው ለጊዜው ነው ልጓማቸው የተያዘው ማለት ነው? ከፖዝ ትርጉም ጋር ካቆራኘነው ይመስላል። ከልጆቻችን ጋር ሆነን በመኪና ወደ አንድ ቦታ ስንሄድ የምንሰማው መዝሙር ወይም የክርስቲያን ሬድዮ ጣቢያ ነው። ወሬ ስናወራ መዝሙሩን አቆመዋለሁ። ወሬያችንን ስንጨርስ፥ unpause አድርገው ይሉኛል። ከቆመበት ይቀጥል ማለታቸው ነው።

ፖዝ ለጊዜው ማቆም ከሆነ አንድ ቀን unpause ይደረጋል ማለት ነው? እነዚህን ነገሮች (ኃጢአት፥ ድኅነት፥ በሽታ፥ ጨለማ፥ ሞት) እንዳስቆማቸው ይቀራሉ ወይስ አንድ ቀን ከቆሙበት ይቀጥላሉ? የተደረጉት pause ከሆነ ይቀጥላሉ ማለት ነው። ምክንያቱም እስከወዲያኛው እንዳይቀጥሉ ከተፈለገ መደረግ ያለበት ፖዝ ሳይሆን ጨርሶ ማስቆም ወይም ማቆም ነው። ለፖዝ የተናገረው ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ከዚህ ትውልድ ላይ ፖዝ ታደርግልኛለህ ሲለው፥ ያንን ያለውን 'ኢየሱስ' እስከመቼ መሆኑን ጠይቆ ይሆን? ያስቆመው እርሱ ከሆነ የሚያስቀጥለውም እርሱ ነው ማለት ይሆን? ወይስ እንዲቀጥሉ ካልፈለገ እርሱ እስከፈለገ ድረስ ሊያስቆማቸው ይችላል ማለት ነው? ይህ ከሆነ ይህን የማድረግ ሥልጣን በእጁ ነዋ!?

ለመሆኑስ እነዚህ ነገሮች እውነት ፖዝ ተደርገዋል? ቆመዋል? ይህ የጠማማና የተዘበራረቀ አተረጓጎም ችግር ነው እንጂ ፖዝ እነዚህን ነገሮች ፖዝ አላደረጋቸውም። ኦርጂናሌው የክርስቶስ ሐዋርያ ጳውሎስም ቀጥ አላደረጋቸውም። የሚደንቀው ነገር፥ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንኳ ፖዝ አላደረጋቸውም። እነዚህ ነገሮች (ድኅነት፥ ኃጢአት፥ ሞት፥ በሽታ፥ ጨለማ) አልቆሙም። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በሥጋ የተገለጠው ታላቁ ጌታ ያላቆመውን ዘበናዩ ሐዋርያ ፖዝ እስኪወለድና እስኪያድግ፥ አገልግሎት እስኪጀምርና እነዚህን መርገሞች በእርሱ 'ሪሞት ኮንትሮል' ጠቅ አድርጎ ቀጥ እስኪያደርጋቸው ድረስ ሲፈስሱ መኖራቸውና አሁን ቀጥ ወይም ለጊዜው ቆም ማለታቸው ይህን ሰው የላቀና ልዩ አያደርገውም? የላቀ ልዩ ሰው የመሆን ጥማት አስቀያሚ አባዜ ነው።

እግዚአብሔር የአገርን ወይም የዓለምን ሁሉ ችግር ፈቺ የሆነ አንድ ሰው ሾሞ አያውቅም። ሰሎሞንም፥ ዳዊትም፥ አዳምም ጳውሎስም ለዚህ አቻ የለሽ ተግባር አልተሾሙም። ዛሬም ያ ሰው ሐዋርያ ፖዝ ሊሆን አይችልም። ነገም፥ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣም በክርስቶስ የሚሾም ሰው የለም። ቃሉ ይህንን አይልም። ስለራሳቸው የገዘፈ አመለካከት ያላቸው ሰዎች በስነ ልቡና ጠበብት pathological egotist ወይም megalomaniacal ይባላሉ። ይህ እዚህ የምናየው አመለካከት ያንን ይመስላል። የትውልድ ታዳጊ እንደሆኑ ራስን መቁጠር የታዳጊነት ወይም የቤዛነት አባዜ ነው። Messiah complex ይሉታል። ይህ ራስን ክርስቶስን የማስመሰል፥ ሥልጣንን የመከናነብ፥ ራስን ቤዛ የማድረግም ጭምር ከጤናማነት የራቀ አመለካከት ነው። ቤዛችን አንድና አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ጌታ ክርስቶስ።

ፖዝ እንደሚነግረን፥ "እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የድህነትን፥ የኃጢአትን፥ የሞትን፥ የበሽታን አካሄድ ፖዝ አርጓል፤ አቁሟቸዋል። እነዚህ ነገሮች በሰው ሕይወት ውስጥ ፍሰታቸው ተከልክሏል።" ግን እውነት ተከልክሏል? አንዱና ብቸኛው ንጉሥ ኢየሱስም በመስቀሉ ላይ ስለ እኛ ተውላጣዊ ሞታችንን ሞቶ፥ ኃጢአታችንን ተቀብሎ ከአብ ጋር አስታረቀን እንጂ ኃጢአትን፥ ድህነትን፥ ሞትን፥ በሽታን፥ የጨለማ ፍሰትን ከዓለም ላይ አላጠፋም። ይህ ቢሆንማ ቀድሞውኑ ቆመዋልና አንድ ዘበናይ 'ሐዋርያ' እስኪነሣና ራሱን እስኪሾም ድረስ 2 ሺህ ዓመታት መጠበቅ የለበትም። ከተነሣና ከተሾመስ ወዲህ ምነው እነዚህ ነገሮች ሁሉ እየፈሰሱ አሉ? ፖዝ እኮ አልተደረጉም! ገናም ጌታ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣና እስኪወስደን ድረስ በጋና ክረምት እንደሚኖሩ እነዚህ ነገሮችም መኖራቸው ይቀጥላል።

ፖዝ አስደራጊው የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱሱ ጌታና መድኃኒት ኢየሱስ እነዚህ ነገሮች ከምድር ላይ እንደሚወገዱ ወይም ተይዘው እንደሚቆዩ፥ ጠቅ ተደርገው ቀጥ እንደሚሉ አልተናገረም። በምድር ሳለን **መከራ** እንዳለብን ነው ያስተማረን። ይህ ሥጋ እስከሚዋጅበት ጊዜ ድረስ በዚህ ሥጋ እስከኖርን ድረስ የውድቀት መዘዞች፥ ጠንቆችና ውጤቶች ይፈራረቁበታል።

**በሽታና ሞት** በፖዝ ፖዝ አልተደረጉም፤ ልንታመም እንችላለን፤ ጌታ መጥቶ ካልተነጠቅን በቀር እያንዳንዳችንም በየተራችን እንሞታለን። በጸጋውና በምሕረቱ ብቻ ከበሽታ ብንጠበቅም እንኳ ሞትን ግን እንሞታታለን እንጂ ሞት ፖዝ አልተደረገም። **ኃጢአትስ?** እንኳን ያልዳኑ ፍጥረታውያን ይቅሩና በበጉ ደም የተዋጀን እኛም በየዕለት ኑሮአችን እየወደቅን የምንነሣ ነን እንጂ ፍጹማን አይደለንም። ፖዝም

አይደለም። ቃሉ ወደ ፍጽምና እንደምናድግ እንጂ ፍጹማን እንደሆንን አያስተምርም።

**ድኅነትስ?** ዛሬ የየዋህ ክርስቲያኖችን ገንዘብ እየመዘመዙ እንደ እንጉዳይ ወይም እንደ ዮናስ ቅል በአንድ ሌሊት ባለጠጋ የሆኑ የዘመናችን ሐዋርያትና ነቢያት ቁጥር ብዙ ነው። እነዚህ ድኅነት እንዳሻራቸው መናገር ይችሉ ይሆናል፤ ጌታ እንዳበለጸጋቸውም በመናገር ሊሸነግሉ ይሞክሩ ይሆናል፤ ግን ይህንን ሽንገላ የሚሉት በንጹሕ ኅሊና ሊሆን አይችልም። ሽንገላ ንጽሕና የለበትም። ተደጋግሞ የተረጋገጠው እውነት እነዚህ ሰብኮ አደሮች በአንድ ጨረቃ ከበርቴ ሲሆኑ የሚያገለግሏቸው ሰዎች ግን ከድጡ ወደ ማጡ የሚወርዱ መሆናቸው ነው።

**የጨለማ ፍሰትስ?** ጨለማውም የንጋቱ ኮከብ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ ይቀጥላል። ዓለማችን ከትናንቱ ዛሬ ብሩኅ እየሆነች ሊመስለን ይችላል፤ ግን አይደለችም።

ይህንን ፖዝ የማድረግ ነገር እንዲያብራራ ተጠይቆ ሲያብራራ ይህን የሚያደርገው በቃል፥ በስብከት መሆኑን ተናገረ፤ ይህ ደግሞ ሌሎች ከሚሰብኩት ቃል ልዩ የሆነው በምን መሆኑ ከቶም አልተነገረም። የቀደሙትን ሰባኪዎች ለማጥላላት ግን ብዙ ብሎአል። ለምሳሌ፥ "ኢዮብን የሚሰብኩ አሉ፤ እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ እያሉ። አሁን እስኪ፥ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ይሰጣል እንጂ ይነሳል?" ሲል ጋዜጠኛዋን ይጠይቃታል። ፖዝ የሚሰብከው እግዚአብሔር መስጠት ብቻ እንጂ ለመንሳት እንዳይችል የተደረገ ሰው ፈጠር፥ ሰው ሠራሽ አምላክ ነው ማለት ነው። የጌታ ሐዋርያ ጳውሎስ መብዛትንና መጉደልን የማያውቅ ሰው ነበር? አልነበረም። ፖዝ፥ "ከመዝሙረ ዳዊት የሚጠቀሱ ጥቅሶች አሁን ኢየሱስን ያሳያሉ? አያሳዩም፤ መዝሙረ ዳዊትን ነው የሚያሳዩት። መዝሙረ ዳዊትን የሚያሳይ ነገር እኔ ማሳየት አልፈልግም፤ ኢዮብን የሚያሳይ ነገር ማሳየት አልፈልግም" እያለ በቃሉ ላይ ሲዘብት ቅንጣት ታህል ፍርሃት አይታይበትም። አለማወቅ የሚያከናንበው ድፍረት ከወኔ ይልቅ ያዳፍራል። ፖዝ ኢየሱስን ብቻ ማሳየት እንደሚሻ ይነግረናል። የሚያስፈራው ነገር ግን የሚያሳየን ኢየሱስ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚነግረን ሌላ ኢየሱስ መሆኑ ነው።

"ኃጢአት፥ ድህነት፥ በሽታ፥ ሞት የሰይጣን መገለጫ ናቸው" ሲል ክርስቲያኖች ከነዚህ ነገሮች የጸዱ ሊሆኑ ይገባል ማለት ነው። ከሞትም ጭምር። ከሞቱ መቼም ሙት ወቃሽ ስለማይኖር አይከሰሱም እንጂ 'ክርስቲያን መሞት የለበትም' የሚል ቅጥፈት የሚሰብኩም ደርዘን ሙሉ አሉን። ጌታ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ ይህች ምድር ምን እንደምትመስል መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልጽ አድርጎ ይነግረናል። ከነዚህ ግልጽ ነገሮች ውስጥ ግን ኃጢአት፥ ድህነት፥ ሞት፥ በሽታና፥ የጨለማ ፍሰት pause እንደሚደረጉ በአንድም ስፍራ አይናገርም። ፖዝ pause እንዳደርግ ነገረኝ የሚለው ኢየሱስ ማን መሆኑ መጠየቅ ያለበት ትልቅ ጥያቄ ነው። በመስቀል ላይ የሞተልን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ እንዲህ የመሰለ ቅሌታም ሹመትና ፌዘኛ ሹም የሚሾም ንጉሥ አይደለም። ታዲያ፥ እንዲህ ያለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኝ pause አድራጊ ሹም የሚሾም ማን ሊሆን ይችላል? መልሱ ግልጽ ነው።

በኢየሱስ የሚመሰል ሰይጣን በሥራ ላይ መሆኑን የረሳንበት ቀን ትጥቃችን የተፈታበት ቀን ነው። ኢየሱስን በማንነቱ ለማወቅ ደግሞ 'ታየኝ፥ ተናገረኝ፥ ተገለጠና ይህን አለኝ፥ ላከኝ፥ ሾመኝ፥ ቀባኝ፥ ሌላም ሌላም' የሚሉንን ሰዎች ሳይሆን በቃሉ ውስጥ ራሱን የገለጠውን፥ የተጻፈውን ያንን ጌታ ነው መስማት ያለብን። ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ጋር ያለን ግንኙነት እንደ ደባል በልክና በድርበብ የሆነ ጓደኝነት ብቻ ከሆነ በተገመዱ ጥቅሶችና 'መገለጥ' በሚሉት ነገር በቀላሉ ልንታለልና ልንወሰድ እንችላለን። ያንን ኢየሱስ ካላወቅነው በሐሰተኛ ኢየሱሶች እንደ ዘበት ተጎትተን ልንወሰድ እንችላለን።

እንደገና ከላይ የጠቀስኩትን ቃል ልድገም፤ *የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።* 2ቆር. 11፥4። ይህ ሐዋርያ የሚያስተዋውቀን ኢየሱስ ድህነትን፥ ኃጢአትን፥ ሞትን፥ በሽታንና ጨለማን ፖዝ የሚያስደርግ ብቻ ሳይሆን የሰይጣን ባሕርይ የተላበሰ ኢየሱስም ጭምር ነው። እንዴው።

# 2. ሰይጣኑ ኢየሱስ?

**ኢየሱስ ሰየጠነ (ወይም ሰይጣን ሆኖ ነበር) ወይ?** ለሚለው ጥያቄ በግልጽ መልስ በመስጠት ፈንታ ዙሪያ ዙሪያውን ሲገደፍር ቆየና፥ ከዚህ በፊትም ያላለውን እንዳለ ተደርጎ እንደተነገረበት አሁን መታተም ባቆመ መጽሔት እንደተጠቀሰ ካተተ በኋላ በጋዜጠኛዋ በእርግጥ ኢየሱስ እንደሰየጠነ ሲጠየቅ፥

> 'ዘላለም ሰይጥኗል ኢየሱስ ትላለህ' ብለው ማቴቱስ ላይ አውጥተውኛል። በመጀመሪያ ደረጃ ያንን ቃል በቀጥታ ኢየሱስ ሰይጥኗል ሚለውን አልተጠቀምኩም። ግን፥ ቃሉ የሚናገርበት እነሱ እንዴት እንዲህ ትላለህ ሲሉ ያልኳቸው፥ 'ይሄ እኮ ማለት ከባድ ነገር አይደለም፤ አየሽ? ክርስቶስ እኔን ሲያስረዳኝ ማለት ነው፥ ስለ ሰዋዊ ማንነቱ አስረድቶኝ ከዚያ በኋላ ስልጠና ሰጠሁኝ ስለ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰዋዊ ማንነት፥ የኖረበት ሕይወት ምናምን፥ ከዚያ በኋላ ሰዎች ጥያቄ አነሱ ምክንያቱም ማንም ያለበትን ዶክትሪን ነው ሚያምነው፤ ተጨቃጨቁ፤ ሄዱ እነሱ። 'ሰው መሆኔ ነው የገረመህ?' አለኝ። 'እርግማን ሆኜ፥ ኃጢአት ሆኜ፥ የግብጽ የበኩር ልጅ ሆኜ ሞቼላቸዋለሁ።' ሆኜ ነው ያለው። አሁንን ይሄንን ሆነ የሚለውን እንዴት ትተረጉሚዋለሽ? ኃጢአት የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለም። የእግዚአብሔር ስብዕና አይደለም። እርግማን የእግዚአብሔር ማንነት አይደለም።

ፖዝ ኢየሱስ እንዲህ አለኝ የሚለው ነገር ከተጻፈው ቃሉ ጋር እኩል ሥልጣን ያለው ተደርጎ ነው የቀረበውና ማብራሪያ የተደረገው። 'ይህንን ምን ትይዋለሽ?' ብሎ ጋዜጠኛዋን ሲጠይቅ ቃሉን አንብቦ፥ 'ይህንን እንዴት ትረጂዋለሽ?' የሚል ነው የሚመስለው። የግብጽ የበኩር ልጅ ሆኜ ሞቼላቸዋለሁ ያለው ማን ነው? ለማን ነው? መቼ ነው? ይህ የመስቀሉ ሞት ነው ወይስ ሌላ? ኢየሱስ የግብጽ የበኩር ልጅ ሆኖ ከሞተ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊትም ሞቶ ነበር ማለት ነው። ሰው ሳይሆን፥ ሥጋ ሳይለብስ በፊትም መለኮት ሞቶ ነበር ማለት ነው። ወይስ ይህ ሌላ ኢየሱስ ነው? ይህ በእርግጥ፥ *ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ* የተባለው ሌላ ኢየሱስ ነው።

> . . . አምላክ እርግማን ይሆናል? አምላክ ኃጢአት ይሆናል? አምላክ የኃጢአት ኔቸር አለው? አየሽ አሁን ችግራችን ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ለኛ ብሎ ማንነቱን ሳይቀይር ነገር ግን ሙሉ ባሕርያችንን ወስዶ የገለጠውን ማንነት፥ 'ኖ! በውስጡ መለኮት ይዞ በሥጋው ሰው ሆኖ እንደዚህ ብሎ [እንላለን ይህ] ቤዛነቱን ፍጹም አያደርገውም።
>
> . . . [ሰየጠነ የሚለውን] ይህንን ቃል የተጠቀሙት ሌሎች ናቸው። የኒ ኬንዮን፥ የሌላ ፌይዝ ላይ ያሉ ሰዎች ያሉት ነው። ግን ያሉትም ቢሆን ብዙ ስሕተት አይደለም። ለምን ብትይ ቃሉን ላሳይሽ፤ . . . የወረደበትን ጥልቀት፥ የወጣበትን ከፍታ፥ አይደለም ኤፌሶን ላይ ያለው? ይህ ከሁሉ በታች ደግሞ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ወደላይ ወጣ። [ጋዜጠኛ፥ ሰየጠነ ካላልክ ለምን ልታሳምነኝ ትሞክራለህ?] እኔ ላሳምንሽ የምሞክረው እዚህ ውስጥ (አእምሮ ውስጥ) ያለውን ባሕላዊ አስተሳሰብ . . . ክርስቶስ ንጉሥ ነው ትያለሽ፤ ክርስቶስ ንጉሥ ብቻ አይደለም፤ እስከ ጥልቅ የወረደ ነው። የወረደበትን ልክ መናገርሽ ምንድነው ክፋቱ? ያልወረደበት ጥግ አለ ወይ? ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሁሉ በታች የወረደው ነው። አሸናፊነት እኮ አይደለም ያ፡ ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሁሉ በታች ወረደ ይላል። መውረዱ ዋጋ እያስከፈለው ነው የወረደው፤ አይደለም? የከፈለውን ዋጋ መናገር ለምን በሃይማኖት አሳብ ላይ ሆነን ለምን እንደ ክፉ አድራጊ ሰዎችን እንከሳቸዋለን?



ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016

ባለቤትነቱን ሳይወስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

ትምህርቱ ተጠምዝዞ እዚያው የተሽከረከረው ቃሉን አላልኩም እያለ ትምህርቱን፥ ማለትም፥ ክርስቶስ ሰየጠነ የሚለውን ትምህርት ግን ስለሚቀበል ነው። የተሰመረውን ዐረፍተ ነገር ልብ ይሏል። 'እነዚያ ኢየሱስ ሰየጠነ ያሉት ብዙም ስሕተት አይደለም' ማለት ብዙ እውነት ነው ማለት ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ሰየጠነ ማለትን በትክክል ይቀበላል ማለት ነው። በእርግጥ ጋዜጠኛዋ እንደሞገተችው ሰየጠነ ካላለ ጉዳዩ በግልጥ እዚያ ላይ መቆም ነበረበት። ግን አይደለም።

> አንቺ ሰለባ የሆንሽበት አንድ አስተሳሰባዊ ዓለም አለ። የዚያ አስተሳሰባዊ ዓለም ሪፍሌክሽን ነው ስሜትሽን የጎዳው። በሌላ መልክ ደግሞ ዓይንሽ ቢከፈት ክርስቶስ የወረደውን ጥግ ክብሬ ነው ብለሽ ዓይንሽ ቢከፈት ያንን ስትይው አታፍሪም? እኔ ስለ ቃል ነው ያወራሁት እንጂ ስለዚያች ነገር አይደለም። አይምሮሽ ውስጥ ግን የተገነባ ነገር አለ። ክብር ሚባለው ነገር ይሄ ነው፤ ውርደቱም እኮ ለኛ ክብራችን ነው።
>
> . . . ኢየሱስ ጴጥሮስን፥ 'ሂድ አንተ ሰይጣን ከበስተኋላዬ' ያለው፤ ይቅርብሽ ብዬ ነበር ግን ልበለው፤ ጴጥሮስ እስኪሰየጥን ድረስ ሄዷል ማለት ነው? ጴጥሮስ እስኪሰጥን ሄዷል? መልሺልኝ። የጴጥሮስ የሕይወት እስታንዳርድ አዘቅት መጠኑ እስኪሰጥን ወርዷል? ኢየሱስ ጴጥሮስን መቤዥ ካለበት ወርዶ እታች ድረስ ማዳን አለበት። . . . ኢየሱስ እንደተናገረው ጴጥሮስ የሰው ልጅ ሆኖ እስከመሰጠን ድረስ ሄዷል? ጌታ ደግሞ ሰውን ለመቤዠት ድንገት ሰው እስከወረደበት ጥግ መውረድ አለበት? ስለዚህ ጴጥሮስ ከሰጠነበት ሁኔታ ለመውጣት ክርስቶስ መሰጠን አለበት? ጴጥሮስ ሰጥኖ ከሆነ? እኔ ያንን ነው ጥልቅ አርገሽ እዩው የምለው። እኔ እስከ እርግማን አምናለሁ፤ እኔ አንቺንም ኦዲየንሱንም ቻሌንጅ የማረገው ፊደሉ ላይ ያለው የሃይማኖተኛና ከንቱ ትሕትና ቋንቋ ለምን እንጠቀማለን? እንዲህ ብለን ብንወስድስ? ጴጥሮስ እስኪሰጥን ድረስ ባሪያ ሆኗል ለሰይጣን? ጴጥሮስን ሰጠነ እስኪያስብለው ድረስ? የሰው ልጅ የውድቀቱ ጥግ መሰጠን እስከሚለው ድረስ ወርዷል? ከወረደ፥ ክርስቶስ ያንን ሰው ለማውጣት መሰይጠን እስከሚለው ቢወርድ ምን ችግር አለው? እኛጋ ነው ሃይማኖታዊ አይምሮ ቃሎቹን ለሚፈልገው ነገር ብቻ መጠቀም ሚፈልገው። ባላፈረበት ነገር አላፈረም። በሆነልኝ ነገር ሆኖልኛል ብዬ ስናገር አላፍርም።

ፖዝ ደጋግሞ የተናገረው የክርስቶስ እርግማንነት ከክርስቶስ መሰይጠን ጋር ሊያቆራኘው የሞከረው ግልብ ስሕተት ነው። 'እርግማን ከሆነ እስከ መሰጠን ቢደርስ ምን ይገርማል?' ያለበት እርግማንና መሰይጠን የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ያጤነውም አይመስልም። ክርስቶስ እርግማን የሆነበትን ሁኔታ ከእርግማን ምንነት ጋር መመልከቱ ተገቢ ነው። በመጀመሪያ የእርግማንን ምንነት መመልከት የተገባ ሲሆን የክርስቶስን እርግማንነት ደግሞ ቃሉን ከጥቅሱ ተፈናቃይ አድርጎ ሳይሆን በገላ. 3 እንደተጻፈው ማየቱ ግድ ነው።

እርግማን ወይም መርገም የሚለው ቃል የጥፋትና የቅጣት ውጤት ተቀባይ መሆንን የሚያሳይ ነው። በብሉይ ኪዳን ቋንቋ እርግማን መጥፎ ቃልን ወይም ብያኔን መናገር ወይም መቀበል (אָרַר አራር)፤ እርም መሆን ወይም እርም መደረግ (חֵרֶם ኼሬም) ማለትም ነው። ሌላው ቃል የክብርና ክብደት ተቃራኒ የሆነ ቅለትን ወይም ቀላልነትን የሚያሳይ קְלָלָה ቅላላህ፤ קָלַל ቃላል የሚል ቃል ነው። መቅለል፥ ውርደት፥ መውረድ፥ መዋረድ ማለት ነው። አማርኛ ሴማዊ ቋንቋ ስለሆነ ይህ ቃል አማርኛም ውስጥ ይገኛል።

ጠቅላላውን ቃል ነው እያየን ያለነውና ስለ እርግማን በመጀመሪያ የምናገኘው በዘፍ. 3 ነው። በዘፍ. 3 አዳምና ሔዋን በመተላለፋቸው ቅጣታቸው የሆነውን ሞት/መለየት ሲቀበሉ እባብ (ሰይጣን) እና ምድር ግን የተረገሙ ሆኑ፤ ቁ. 14 እና 17። እባብ ቀድሞም የወደቀ ፍጡር ነበርና የተጨመረ ፍርድን ተቀበለ። በአዳም ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚስቱን ቃል መስማትም የተነሣ ምድር ተረገመች፤ የድካሙና የጥረቱ ምክንያት ሆነች። ከሰዎች መጀመሪያ ሲረገም የምናገኘው ወንድሙን የገደለ ቃየን ነው፤ ዘፍ. 4፥11። ከእርግማኑ ጋር የተያያዘውም የምድር በረከቷን ማገድ እና ተቅበዝባዥነቱ ናቸው። እርግማን እንግዲህ ፍርድ፥ ቅጣት፥ ብያኔ፥ የጥፋት ውጤትን መቀበል፥ ከከበረ ስፍራ መውረድና መዋረድ ነው።

አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረን በቀደመው አባታችን በአዳም ሁላችንም ተኮንነናል፤ በክርስቶስ ግን ጻጋው አጽድቆናል፤ ሮሜ. 5፥15-21። ስለዚህ ከክርስቶስ ውጪ ያለ ማንም ሰው ከእርግማን በታች ነው። አዲስ ኪዳን እርግማን የሚለው ይህንን በብሉይ ኪዳንን ሕግ ሥራ ጸንቶ አለመቆምን ነው፤ ገላ. 3፥10-13። ማንም ሰው ወደ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ግን ክርስቶስ ሕግን ፈጽሞ በምትካችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ይህንን እርግማን ስለሻረው ነጻ ሆኖአል።

ወደ ክርስቶስ መረገም ወይም እርግማን መሆን እንምጣ። ቃሉ በገላ. 3፥13 ነው የተጻፈው። ፖዝ እንደሚያደርገው ጥቅሱ ከስፍራው እንዳይፈነቀል ጠቅላላውን የገላትያን መጽሐፍ አሳብ መረዳት ተገቢ ነው። የገላትያ መልእክት የተጻፈላቸው ሰዎች ገላትያ በሚባል ሰፊ አውራጃ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ናቸው። በሁለተኛው የወንጌል ጉዞው ጳውሎስ ወንጌልን ሰበከላቸውና በ3ኛው ጉዞው እያጸናና እያበረታቸው በዚያ አለፈ። ከገላትያ መልእክት እንደምንረዳው እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ አምነው ከዳኑ በኋላ ወደ ልዩ ወንጌል ፈጥነው አለፉ፤ ገላ. 1፥6። ይህ ልዩ ወንጌል በክርስቶስ ከዳኑ በኋላ ወደ መገረዝ (መገረዝ የብሉይ ኪዳን መታወቂያ ስለሆነ ሕግን ወደ መጠበቅ ማለት ነው) እንዲመለሱ ያስተማሩ ሰዎችን ትምህርት ተቀብለው ሕገኞች ሆኑ። ሕግ ወደ መጠበቅ፥ ወደ መገረዝ፥ ቀኖችና ወራትን ወደመጠበቅ፥ ወደ ባርነት ወረዱ፤ 4፥1-10።

በሕግ መጽደቅ ቢቻልማ ኖሮ ክርስቶስ መምጣት፥ ሥጋ መልበስ፥ ስለ እኛ መሞት ባላስፈለገውም ነበር። ሕጉን ጠብቆ መዳን ይቻል ነበራ! ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ኢየሱስ ይህንን እውነት ነው አድምቆ እየጻፈላቸው ያለው። ጌታ ያገለገለበትን ዘመንና የሕግን ምንነት አስተውለን እንረዳ። እኛ ከሕግ በታች እንዳንሆን እርሱ ከሕግ በታች ተወለደ። እኛ ከሕግ በታች አይደለንም፤ እንዳንሆን ያደረገን ደግሞ ስለእኛ ከሕግ በታች ተወልዶ፥ ሕግን ሁሉ ፈጽሞልን፥ ከሕግ እርግማን የዋጀን ጌታ ነው። በመስቀሉም አዲሱን ኪዳን አቆመ።

ነጻነት፥ ቤዛነት፥ ዋጋ ይጠይቃል። ጌታ እኛን ከሕግ ቀንበርና እርግማን ነጻ ያወጣን ነፍሱን ከፍሎ ነው። ሕግ በራሱ ምንም ክፋት የለበትም፤ ጻጋው እንዲያድነን ኪዳኑ እስኪፈጸም በእምነት ወደ እግዚአብሔር መቅረቢያው ሆኖአል። አዲሱ ኪዳን በደም ሲመረቅ ግን ቦታውን ጻጋው በእምነት እንዲያድነን ለቀቀ። በጻጋው የመዳናችን ዋጋውም ደሙ ነው። የኛ ከሕግ እርግማን አርነት መውጣት በዋጋ የተገኘ ነው። ይህ የተፈጸመው ከሕግ በታች መሆን የሌለበት እርሱ ለኛ ሲል ከሴት ተወልዶ፥ ከሕግ በታች ተወልዶ፥ በእንጨት ተሰቅሎ ከሕግ እርግማን ስለዋጀን ነው።

ጳውሎስ በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን ቃል ጠቅሶ የተናገረው እውነት ከሕግ በታች መሆን ከእርግማን በታች መሆንን ነው። *ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና* (ቁ. 10)። ክርስቶስ ደግሞ ከዚህ እርግማን የዋጀን ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ነው፤ *በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤* (ቁ. 13)።

ይህ ቃል 'ተብሎ ተጽፎአልና' የተባለው በዘዳ. 21፥22-23 የተጻፈው ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ፥ እንዲሞትም ቢፈረድበት፥ በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው፥ በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጠህን ምድር እንዳታረክስ በእርግጥ በዚያው ቀን ቅበረው። የሚል ቃል ነው። ኃጢአተኛው በተሰቀለ ጊዜ እርግማኑን ተሸክሞ ነው በግላጭ



ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥
የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

የተሰቀለው። ሲሞትም እንደተሸከመው ሞቶአል። አይሁድ ሰዎችን በሞት ሲቀጡ ወግረው እንጂ ሰቅለው ስለማይገድሉ፥ ይህ መሰቀል የሬሳ ሰቅሎ እንደ መቀጣጫ ማሳየት ሳይሆን የቅጣት ከሆነ የከፍተኛ ውርደት ሞት ነው። የእርግማን ሞት ነው። በእንጨት የሚሰቀል የተረገመ ነው።

በጌታ ዘመን ደግሞ የሮማውያን የመጨረሻው የከፋ ቅጣትና የውርደትና የእርግማን ሞት የመስቀል ሞት ነው። ጳውሎስ ያያያዘው የክርስቶስ እርግማን መሆን ይህ ስለ እኛ የሞተው ሞት ነው። ጳውሎስ በገላ. 3፥10-13 የጠቀሳቸው ሁለት የተረገሙ ክፍሎች ይገኛሉ፤ አንዱ ሕግን ጠብቀው መዳን ያልቻሉት፥ በሕግ መጽሐፍ በተጻፈው ጸንተው የማይኖሩትና የማያደርጉት ናቸው። ይህ ሰውን ሁሉ የሚሸፍን እርግማን ነው። ማንም ሕግን ፈጽሞ ተጠንቅቆ ጠብቆ የዳነ ፍጹም ሰው የለም። ስለዚህ ሕጉ እኛንም ጨምሮ ሁሉንም ከእርግማን በታች ያስቀምጠዋል። ሁለተኛው ክርስቶስ ነው። እርሱ ደግሞ ሕግን ሁሉ ስለ እኛ ፈጽሞ በፈንታችን የተሰቀለውና እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ወይም ኩነኔ ወይም ፍርድ የዋጀን ነው።

ጌታ በመስቀል ላይ የተሸከመው የራሱ ኃጢአት አልነበረውም። የራሱ እርግማንም አልነበረውም። ነገር ግን የእኛን ኃጢአት በመውሰድ በፈንታችን፥ በምትካችን በመሞት በእንጨት የተሰቀለው እርግማን ሆነ። ይህን በማድረግም ዋጀን፤ ሙሉ ዋጋ ከፍሎ መልሶ ገዛን። ጌታ ስለ እኛ እርግማን የሆነው፥ በእንጨት ላይ የሚሰቀል የተረገመ እንደሆነ ሆኖልን የእኛን ኃጢአት በመስቀል ላይ በመሸከሙ ነው። ጴጥሮስም በ1ጴጥ. 2፥24 *ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤* ይለናል። ክርስቶስ ኃጢአታችንን በእንጨት (በመስቀል) ላይ መሸከሙ የኛን እርግማን የተሸከመ ሰው የሆነ አምላክ እንጂ ሰይጣን አያደርገውም።

ፖዝ በግልጥ ያልተናገረውና ጋዜጠኛዋም በስሱ የጴጥሮስን አሳብ ምንነት ከመናገር ባለማለፍ እንዲገልጥ ያላደረገችው ነጥብ፥ 'በእርግጥ ጴጥሮስ ሰይጥኖ ነበር ወይ?' የሚለው ነው። እንደ ፖዝ ሰፊ ግን ግልጽ ያልሆነ ማብራሪያ ጴጥሮስ የሰየጠነ ሲሆን ኢየሱስ ጴጥሮስን ከሰየጠነበት ለማውጣት መሰይጠን ኖሮበታል ማለት ነው። በተድበሰበሰ ቋንቋ የተላለፈው አሳብ ይህ ነው።

> እኔ እስከ መሰጠን ድረስ ወርጄ ከሆነ ክርስቶስ እኔን ለመቤዠት እስከ መሰጠን ሊመጣ ይችላል። ወርጄ ከሆነ። ሲያል ወርዷል አይደለም? የወረዱ ስላሉ እንጂ ስለተሸነፈ ነው? የሰው ልጆች ኃጢአት ስለከበደው ነው ሲያል የወረደው? የወረዱ ስላሉ የወረዱትን ለማውጣት አይደለም? እዚያ ጥግ ድረስ ሲወርድ እኛ እስከ መሰጠን ዘር ወርደን ከሆነ መውረድ ግዴታው ነው። . . . [መሰይጠንን] ለምን ይህንን ቃል በስድብ መንፈስ ተረዳሽው? ለምን የመውረዱን ጥልቀት አትረጂውም? ለምን እዚያጋ [እርግማንጋ] በቃሽ? እርግማን ላይ ስለደረስን ነው ክርስቶስ እርግማን የሆነልን፤ ኃጢአት ላይ ስለደረስን ነው ክርስቶስ ኃጢአት የሆነልን፤ በሽታ ላይ ስለደረስን ነው የተገረፈው፤ ድህነት ላይ ስለደረስን ነው ድኃ የሆነው፤ ድኅነት ብቻ ቢሆን ድንበራችን እዚያ ላይ ይቆም ነበር፤ መሰጠን ላይ ደርሰን ከሆነ ቢሰጥን ምን ችግር አለው? ደርሰን ከሆነ፤ ከሆነ ነው የምልሽ።
>
> . . . ይሄ ፊደል [ሰየጠነ የሚለው] አንቺጋ ረክሶአል፤ እኔጋ አልረከሰም። ጴጥሮስን እስከመሰጠን ያወረደ ቃል ካለ ጴጥሮስን ለመቤዠት ጌታዬ ልክ እርግማን እንደሆነ እዚህ ድረስ ወረደ ብል ኢየሱስ ሰይጣን ነው እያልኩ አይደለም፤ ሊቤዠው ሰውየው እስከወረደበት ጥግ ወርዷል እያልኩ ነው። አይምሯችን ውስጥ ግን ፊደሉ ረክሷል፤ ስለረከሰ፥ 'እንዴት ለጌታዬ ይህን እላለሁ [ሴጠነ እላለሁ] ብለሽ ፊደሉ ላይ ሙግት ጣልሽ ማለት ነው። ፖይንቱ ክርስቶስ እርግማንም የሆነው፥ ኃጢአትም የሆነው፥ በሽታም የተሸከመው፥ ድኃም የሆነው፥ ሁሉንም የወረድነውን ጥግ ለመሸፈን ነው።

ፖዝ ከላይ በተወሰደው ክፍል ከጋዜጠኛዋ ጋር በከረረ ክርክር መሃል ነው እነዚህን ነገሮች የተናገራቸው። በመጀመሪያ፥ በግልጽ ክርስቶስ ሰየጠነ አላልኩም እያለ ያሉትን ሰዎች ትክክል ናቸው ካለ ምንም ልዩነት የለውም። እርሱ ሊል የፈለገውንና በቀጥታ ሊል ወኔና ድፍረት ያጣበትን አሳብ ወክለው እነዚያ ካሉለትና ይህ አባባላቸው ከተስማማው ይህ የቃል ሳይሆን የአቋም ጉዳይ ነውና ተስማምቶበታል ማለት ነው። ሰውየውና እንደራሴው የተናገረው ደግሞ አንድ ነውና እርሱ እራሱ እንዳለው በእርግጥ መቁጠር ይቻላል። ሁለተኛ ደግሞ በጥያቄ እንጂ በአቋም ደረጃ ግልጽ አድርጎ ያልተናገረውና 'ሰው እስከ መሰይጠን ደርሶ ከሆነ' ብሎ ሳይገልጥ የዘለለው፥ ጋዜጠኛዋም በግልጽ ያልጠየቀችው አቋሙ የጴጥሮስ ወይም የሰዎች መሰይጠን ክርስቶስ እነርሱ የወረዱበት ጥግ ወይም እስከ መሰይጠን ድረስ አድርሶታል የሚል ነው። ንግግሩ 'ምን ያስገርማል? በሚል ሻሽ ቢሸበብም ቃሉ አቋሙን ያሳያል።

ኢየሱስ ሰይጣን ሆነ ወይም የሰይጣንን ባሕርይ ተላበሰ የሚለው ትምህርት በፖዝ የተጀመረ አይደለም፤ በእርሱም አይደመደምም። ፖዝ የሚነዛው የትምህርቱ ዋና አቀንቃኝ የሆነውን አሜሪካዊውም ዊልያም ኬንየንን መርዘኛ ትምህርት ነው። ከላይ ባየነው በተናገረው ክፍል ራሱ የጠቀሰው ኬንየን ይህንን የሐሰት ትምህርት ካናኙት ሰዎች አንዱ ነው።

ከዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ በፊት በWilliam Kenyon በኋላም፥ በተለይም ከቃል-እምነት አስተማሪዎች መካከል Kenneth Hagen, Kenneth Copeland, Frederick Price, Benny Hinn እና ሌሎችም ይህንን ትምህርት አስተምረውታል። ቤኒ ሂን፥ 'He [Jesus] who is righteous by choice said, "The only way I can stop sin is by Me becoming it. I can't just stop it by letting it touch Me; I and it must become one." Hear this! He who is the nature of God became the nature of Satan where He became sin! ብሎ ነበር።[2] ጻድቁ ኢየሱስ ነው ይህን እንዳለ ቤኒ ሂን የተናገረው፥ 'ኃጢአትን ማስቆም የምችልበት መንገድ አንድ ብቻ ነው፤ ያም እኔ እርሱን በመሆን ነው፤ ኃጢአት እንዲነካኝ በመፍቀድ ሳይሆን እራሱን በመሆን ነው፤ ይህን ስሙ፤ የእግዚአብሔር ባሕርይ የነበረው ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ በመውሰድ ኃጢአት ሆነ።' ይህ የቤኒ ሂን ትምህርት ነው። ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ መውሰዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም።

የቃል-እምነት አስተማሪዎች፥ 'ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ ስለተጋራ ዳግም መወለድ አስፈልጎት ነበር፤ በሞቱና በትንሣኤው መካከል ነው ይህን ዳግም ልደት ያገኘው' ይሉናል። በአገላለጣቸውና ግልብ በሆነ ቋንቋቸው ይህንን የሦስት ቀን ቆይታውን፥ ኢየሱስ እንዴት በሰይጣን መረብ እንደተያዘ፥ እንዴት እየተጎተተ በፊቱ እንደቀረበ፥ እንዴት በባለ ሦስት ቀስት መውጊያዎቻቸው እየጎነተሉትና እየወጉት እንደተሳለቁበት፥ ሲገልጡት በስፍራው አብረውት የነበሩ የዓይን ምስክሮች ይመስላሉ።

ፖዝ እንደነዚህ ሰዎች ገላጭ ቋንቋ አልተጠቀመም፤ እንዲያውም በግልጽም 'ሆነ' አላለም። "ቢሆን ምን ያስገርማል?" ነው ያለው። ይህ ስልቻና ቀልቀሎ ማለት ነው። ኢየሱስ ሰይጣን ቢሆን ምን ያስገርማል? ሞርመኖች ኢየሱስ የሉሲፈር መንፈሳዊ ወንድም ነበር ይላሉ። እኛም ጭምር እንደዚያ መሆናችንን ይነግሩናል። ኢየሱስና ሰይጣን ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ናቸው ማለታቸው ነው። ኢየሱስ ሰው የሆነው የሰውን ሰውነት በሥጋና ደም ለመካፈል በሥጋው ኃጢአታችንን ለመሸከም፥ በደሙም የበደላችንን ስርየት ለመፈጸም ነውና ሰይጣንም የሆነው የወንድሞቹን የሰይጣናትን ኃጢአት ሊሸከም ከሆነ አጋንንትም ድነዋላ?! እናም አጋንንት በደኅንነት በኩል

[2] በፈረንጆች በ12/1/90 በTBN ቲቪ ከቀረበው ትምህርቱ።


ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥
የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

ወንድሞቻችን ናቸዋ?! ከኛ ጋር ተደባልቀው በቤተ ክርስቲያናችን እየተገኙ የድንቆችና ምልክቶች ርችት እየተኮሱ ቢያጅቡን ሊያስደንቅ የተገባው ነገር አይደለማ?! ኢየሱስ ሰይጣን ቢሆን እንዴት አያስገርምም?! ዛሬ ሐሰተኛ ድንቆችና ምልክቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰይጣን እንደማይደረግ ምን እርግጠኛ ያደርገናል? ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል፤ 2ቆሮ. 11፥14።

ኢየሱስ ሰይጣን ቢሆንማ ያስገርማል እንጂ! ኬነት ሄገን፥ ቤኒ ሂን ወይም ቡችሎቻቸው ፈጥረው አስተማሩት እንጂ ይህ ቃሉ የማያስተምረው የተፈጠረ ነገር ነውና፥ የተፈጠረ ተረት ሲደመጥ ያስገርማል እንጂ ለምን አያስገርም! ፖዝ የሚያሰማን፥ 'ቢሆንስ ምን ያስገርማል?' ወደ ሰይጣን ጎራ የምታስገባ ታናሽ እርምጃ ናት፤ ግን ከትንሿ እርምጃ ቀጥሎ ትልቅ ዝላይ መጠበቅ እንችላለን። ይህ ያፈጠጠ የስሕተት ትምህርት ነው።

'ቢሆንስ ምን ያስገርማል?' ብሎ እርግጠኛ የማያስመስለውን የተደፋፈነ ቃል ከመናገር ይልቅ በግልጽ ቋንቋ፥ ኢየሱስ ወደ ሰይጣንነት የወረዱ ሰዎችን ሊያድን ሰይጥኖአል ቢልና እርግጠኛ ትምህርቱን ገሃድ ቢያደርግ የትምህርቱ ምንጭ ይገለጣል። ወይም፥ 'የለም አልሰየጠነም' ቢልም ክርክሩ በቆመ ነበር።ኢየሱስ ሰይጥኖአል ወይም አልሰየጠነም እንጂ ቢሰየጥን ምን ያስገርማል ማለት ማምታታትና ማጭበርበር ነው። ፖዝ የነኬንየን እና የነሄገን ደቀ መዝሙር እንደመሆኑ መጠን ይህንን ትምህርት በግልጽና በአማርኛ እንዲናገር ይጠበቅበታል።

ለመሆኑ፥ በእውን ጴጥሮስ ራሱ ሰይጥኖ ነበር ወይ? እስኪ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ የተጻፈውን በጥሞና እንመልከት። በማቴ. 16፥ 23 ላይ፥ እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፦ ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው ብሎታል። እዚያው ቁጥር 18 ላይ ደግሞ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም ብሎታል። እንግዲህ የዮና ልጅ ስምዖን ጴጥሮስ ወይም ዓለት ነው? ወይስ ሰይጣን? ወይስ እነዚህ ስሞች መግለጫዎች ናቸው? ጴጥሮስ 'ዓለት' የተባለው፥ 'አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ' በማለቱ እንጂ ድንጋይ ስለሆነ አይደለም። እንደዚሁ ሁሉ፥ 'ሰይጣን' የተባለውም፥ አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ስለጀመረ ነው እንጂ ጴጥሮስ በዚያች ቅጽበት ወደ ሰይጣንነት ተለውጦ ስለነበረ ወይም ስለሰየጠነ አይደለም። አይሁንብህ፥ ይህ አይደርስብህም ያለው ጌታ ክርስቶስ መከራ እንደሚቀበል እንደሚሞትና እንደሚነሣ ሲናገር ነው። ጌታ የመጣበትና ደጋግሞ ይናገር የነበረው ዋና ግቡ ይህ ነበር። ይህንን አውቆም ይሁን አዝኖለት በጥብቅ መቃወም የእግዚአብሔርን አሳብ መቃወም ነው። የእግዚአብሔርን አሳብ መቃወም ደግሞ የሰይጣንን አሳብ ማገልገል ነው። የሰይጣንን አሳብ ማገልገል ሰይጣንነት አይደለም፤ የእግዚአብሔርን አሳብ ማገልገል እግዚአብሔርነት እንዳልሆነ ሁሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በመሰለ ገላጭና ስዕላዊ ቋንቋ የተሞላ ነው። ለምሳሌ፥ 'እናንተ የእፉኝት ልጆች' (ማቴ. 12፥34፤ 23፥33)፤ ወይም፥ 'ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው' (ዮሐ. 6፥70)፤ ወይም፥ 'እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ' (ዮሐ. 8፥44)፤ ሲል ተመሳሳይ ቋንቋ መጠቀሙና የሰዎቹን ግብር ማመልከቱ እንጂ በቀጥታ እነዚያ ሰዎች እነዚያን ነገሮች ናቸው ማለት አይደለም። ጴጥሮስ ሰይጣን አልሆነም፤ ሰይጣንም አልገባበትም። ቢገባበትማ ያወጣለት ነበር እንጂ ሰይጣን የገባበትን ወይም ሰይጣን የሆነ ሰውን የመንጋው ሹም አያደርገውም ነበር።

'ጴጥሮስን ለማዳን እስከ መሰይጠን ቢደርስስ?' ከተባለ፥ ዳዊት ራሱን የሞተ ውሻን ወይስ ቁንጫን ታሳድዳለህን? ብሎ ለሳኦል ተናግሮ ነበር (1ሳሙ. 24፥14)። ጌታ ዳዊትን ለማዳን የሞተ ውሻ ወይም ቁንጫ ሆነ ሊባል ነዋ!? ወይም በሌላ መሢሓዊ መዝሙር (መዝ. 22) እኔ ግን ትል ነኝ፤ ሰውም አይደለሁም ብሎአልና ጌታ ምናልባት ትል ቢሆንስ ሊባል ነዋ!? እንደ ጭንጋፍ የሆነውን ጳውሎስን ሊያድን ጭንጋፍ ሆኖ ቢሆንስ ሊባል ነዋ!? እንዲህ ያለውን መመሳሰል ብንፈልግ ማለቂያ ወደሌለው ተረት እንወርዳለን። በየዘመናቱም ለሚፈጠሩት የሰይጣን የተራቀቁ ስሕተቶች ማለቂያ አይኖራቸውም።

ፖዝ ጴጥሮስን ወይም ኢየሱስን ማሰይጠኑ ወይም ሰይጣን ማድረጉ የከፋ የስሕተት ትምህርት ነው። ኢየሱስ ሰየጠነ ወይም አልሰየጠነም ማለትን በቃለ መጠይቁ ላይ በግልጥ መናገር እየቻለ ጋዜጠኛዋን ለማደናገር እየሞከረና እያምታታ ቢያልፍም በትክክል እንደሚያምንበት ግልጽ ነው። 'እኔ ያልኩት፥ እስከዚያ ቢወርድ ምን ያስገርማል? ነው እንጂ ሰጠነ አላልኩም፤' ሊል ይችላል። ነገር ግን፥ እነዊልያም ኬንየን ኢየሱስ ሰየጠነ ያሉትን የሐሰት ትምህርት፥ 'ብዙም ስሕተት አይደለም' ብሎአል።

የኤሴክ ዊልያም ኬንየን (E. W. Kenyon) ትምህርት በግልጽ፥ ኢየሱስ እኛ የነበረንን የሰይጣን ባሕርይ ተካፋይ እንደሆነ፥ በሲዖል ዳግም ልደትን አግኝቶ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፥ የኛም አዲስ ፍጥረትነት ከዚያች ጊዜ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። እኛ ሰይጥነናል፤ ኢየሱስም የእኛን ባሕርይ ሲካፈል፥ በሥጋና ደም እኛን ሲመስል ሰይጥኖአል የሚል ነው። መስቀሉን ፋይዳቢስ ሲያደርግ ኬንየን መስቀሉን ደኅንነታችን የተፈጸመበት ሳይሆን 'የሽንፈት ስፍራ' ይለዋል። “We have sung `Nearer the cross' and we have prayed that we might be `Nearer the cross' but the cross has no salvation in it. It is a place of failure and defeat.”[3] እንዲህ የመሰለው ትምህርት 'ብዙም ስሕተት የለበትም' ከተባለና እንደ ፖዝ ስሕተቶችና እውነቶች በብዙ እና በጥቂት ስሕተቶች ወይም በድምጽ ብልጫ የሚለኩ ከሆነ ምንም እርግጠኝነት በሌለው ሕይወት እንመላለሳለን ማለት ነው። ማንም ዳግም የተወለደና በመጽሐፍ ቅዱስ እውነትነት የሚያምን ክርስቲያን በእንዲህ ያለ ብዥታና የቀለለ ትምህርት ውስጥ አይዳክርም፤ አይዋዥቅም።

የኢየሱስን ሰይጣንነት ከተናገሩት መካከል ቤኒ ሂን እንዲህ ብሎ ነበር፤

> The serpent is a symbol of Satan. Jesus Christ knew the only way He would stop Satan is by becoming one in nature with him. . . . He did not take my sin. Sin is the nature of hell. Sin is what made Satan. . . . It was sin that made Satan. Jesus said, "I'll be sin! I'll go to the lower place! I'll go to the origin of it! I won't just take part in it, I'll be the totality of it." When Jesus became sin, sir, He took it from A to Z and said, "No more!" Think about this: He became flesh that flesh might be like Him. He became death, so dying men can live. He became sin so sinners can be righteous in Him. He became one with the nature of Satan, so all those who had the nature of Satan can partake the nature of God.[4]

ይህን ክፍል ጠቅላላውን ሳይሆን የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ክፍል ብቻ ልተርጉመው፤ 'እባብ የሰይጣን አምሳያ ነው። ኢየሱስ

[3] *Kenyon, E. W.* Advanced Bible Course, *E W Kenyon Publisher, 2004, p.279.*

[4] *Hannegraaf, Hank.* Christianity in Crisis, 21st Century, Thomas Nelson, 2012, p.172-3.


ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥
የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

ክርስቶስ ሰይጣንን የሚያስቆምበት ብቸኛ መንገድ ከእርሱ ጋር በባሕርይ አንድ በመሆን መሆኑን አውቆአል። . . . ከሰይጣን ጋር በባሕርይው አንድ ሆነ፤ ይህም የሰይጣን ባሕርይ የነበራቸው ሁሉ የእግዚአብሔር ባሕርይ ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ነው።"

ኬነት ሄገን ስለ ኢየሱስ መሰይጠን ሲናገር፥ "Spiritual death means something more than separation from God. *Spiritual death also means having Satan's nature. . . .* Jesus tasted death-spiritual death-for every man."[5] "መንፈሳዊ ሞት ማለት ከእግዚአብሔር ከመለየት ያለፈ ነገር ነው። መንፈሳዊ ሞት የሰይጣንን ባሕርይ መውረስም ነው። ኢየሱስ ስለ እያንዳንዱ ሰው ሞትን፥ ማለትም መንፈሳዊ ሞትን ቀመሰ።" ይላል ሄገን። የሰይጣንን ባሕርይ ወረሰ ሰየጠነ ማለት ነው። የሚያሳዝነው ነገር፥ እነዚህ ሰዎች የሚሉት ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ ወረሰ የሚሉት ነገር ያልተጻፈና የተፈጠረ ነገር መሆኑ ነው። ያልተጻፈውን ነገር ልክ እንደተጻፈ አድርገው ነው የሚናገሩትና መጽሐፍ ቅዱስን የማያነብቡትን የማያስተውሉ ሰዎች የሚያወናብዱት።

Fred Price የተባለው ከሄገን ደቀ መዛሙርት አንዱ የመምህሩን ስሕተት የሚያስከነዳ ነገር በመናገር ኢየሱስ መንፈሳዊ ሞትን የሞተው ወይም ወደ ሰይጣንነት የተለወጠው በትክክል የት እንደነበርም ሊያስረዳ ሲሞክር እንዲህ ይላል፤ "Somewhere between the time He was nailed to the cross and when He was in the Garden of Gethsemane-somewhere in there-He died spiritually. Personally, I believe it was while He was in the garden."[6] በመስቀል ላይ በመቸንከሩና በጌቴሴማኒ አትክልት ስፍራ መካከል ባለው ጊዜ፥ እዚያ መሐል ላይ ነው መንፈሳዊ ሞትን የሞተው። እኔ በግሌ እንደማምነው፥ በአትክልቱ ስፍራ ነው የሞተው።" መንፈሳዊ ሞት መሞት ማለት ከላይ ያየነው ሄገን ኢየሱስን ሰየጠነ ወይም የሰይጣንን ባሕርይ ወረሰ ያለበት ቋንቋ ነው።

ቤኒ ሂን፥ ሄገን ወይም ፕራይስ ኢየሱስ የሰይጣንን ባሕርይ ያዘ ብለው እንዲህ ያለ ቅጥፈት በድፍረት ይናገራሉ። ፖዝ የነዚህን ሰዎች መርዛማ አስተምህሮ እያኘከ ኖሮ ነገር ግን እንደነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች በግልጥ ሊናገር ያልደፈረውና ዳር ዳር እያለ ያለው በአገሪቱ ያለውን ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ተግዳሮት በመፍራት፥ ያለዚያም ወኔ እስኪቀዳጅና በድፍረት ለመናገር ምቹ ጊዜ በማድባት እየተጠባበቀ ይመስላል።

## 3. ሰውየው ኢየሱስ?

**ኢየሱስ እንደ ሰው ብቻ ነው የተመላለሰው?** ፖዝ ይህን በግልጽ ተናግሮአል። ይህ ጠማማ የስሕተት ትምህርት ኢየሱስ በምድር በተመላለሰባቸው 33 ዓመታት ከቶም አምላክነቱን አልገለጠም፥ አልተለማመደም፥ "በምድር ሲመላለስ የመለኮትን ኃይል አልተጠቀመም" እንደ ፍጹም ሰው ብቻ ሆኖ ነው ትምህርቶቹን ያስተማረውና ተአምራቱንም ያደረገው የሚል ሆኖ እኛም እንደ እርሱ ፍጹም ሰው በመሆን እነዚህን እናደርጋለን ወደሚል ድምዳሜ የሚያመራ ስሕተት ነው።

ወደ ምድር ሲመጣ፥ ፊልጵስዩስ ምን አለ? በምስሉ እንደ ሰው ተገኘ፤ ራሱን አዋረደ፤ ራሱን ባዶ አደረገ፤ የባሪያን መልክ ይዞ ለሞት ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ። ሙሉውን ቅድምም እርግማን ሆነ የሚለውን እዚህ ላይ ማምጣት ትችያለሽ። ለሞት፥ ይኸውም የመስቀል ሞት፤ እሷ ፊደል ናት ኋላ የምመልስልሽ። አሁን ክርስቶስን ላሳይሽ፤ ሰው ሲሆን ክርስቶስ ሁለተኛ አዳም ነው የሆነው። እግዚአብሔር ሆኖ አይደለም በምድር የተመላለሰው። እግዚአብሔርነቱን እያሳየ አይደለም በምድር የሠራው።

ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ፥ ማንነቱ የማይቀየር [በመካከል ጋዜጠኛዋ በምድር ሲመላለስ ክርስቶስ መለኮትነቱን ገልጧል? ተጠቅሟል? ብላ ትጠይቀዋለች] ገልጧል፥ ተጠቅሟል፤ አልተጠቀመም ብዬ ነው የማምነው። [እዚህ በግልጽ የተዘበራረቀ የተጋጨ ቃል ነው የተነገረው ቢሆንም ሲያብራራ] ክርስቶስ በምድር ላይ መለኮታዊ ማንነቱን አልተጠቀመም። የተመላለሰው በሰው ማንነት፥ በመንፈስ ቅዱስ ቅባትና ኃይል ነው።

ጋዜጠኛዋ ደጋግማ ያቀረበችውን የኃጢአት ስርየት መስጠት እና አብሮት ለተሰቀለው ሰው፥ 'ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ' የሚለውን ቃል በመንገር እነዚህ የመለኮት ባሕርያት መሆናቸውን ልታሳይ ብትጥርም፥ ይቅርታ ማድረግ ለተከታዮቹም የተሰጠ ሥልጣን መሆኑን እና በመስቀል ላይ የተሰቀለው እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማመኑ ሊያስገባው እንደቻለ፥ እኛም የዳንነው 'በዚያ ፕሪንሲፕል' መሆኑንና እርሱም ራሱ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ እንደሚችል ሊያስረዳ ሞክሮአል።

> . . . ኢየሱስ አምላካዊ ኃይሉን እየተጠቀመ ከሆነ እየሠራ ያለው፥ እኛ አሁን በመንፈስ ቅዱስ የምንኖረውን ኑሮ መሥራት አንችልም ማለት ነው። . . . [ጋዜጠኛ፥ እኔ ክርስቶስ መለኮት መሆኑን አምናለሁ] እነማን ያምናሉ? መጽሐፉ ይላል ወይ? እነማን መለኮት ነበር ይላሉ? የአምላክ እናት የሚሉ እኮ አሉ፤ . . . ኃጢአት ማሰረይ ይችላል ወይ ሰው ላልሽው መልሱ አዎን ነው። ለምን አዎ ሆነ? ጌታ ኢየሱስ እዚያው አንቺ የጠቀስሽው ጥቅስ ላይ ሲናገር እስራኤሎች የተቆጡበት ላይ ሲናገር ምንድነው ያለው ጌታ ኢየሱስ፥ 'የሰው ልጅ ኃጢአትን ማሰረይ እንደሚችል እንድታውቁ' [ጋዜጠኛ፥ የሰው ልጅ ያለው ስለራሱ ነው] የሰው ልጅ ማንን ወክሎ ነው ያለው? በአብ ቀኝ የተቀመጠ ስብዕና አይደለም የሰው ልጅ የተባለው? . . . ክርስቶስ ኃጢአትን አሰረየ የምንልባቸው ነገሮች አምላካዊ ማንነትን ኣያሳዩም። . . . አንዳንዶች ስግደትን ተቀብሏልና አምላክ ነው ይላሉ፤ ለዳዊትና ስሎሞንም ተሰግዶአል። . . . አንዳንዶች በውኃ ላይ ሄዶአል ይላሉ፤ ስንቶች አስማተኞች አሉ በውኃ ላይ የሚሄዱ . . . መለኮት ናቸው ወይ? . . . የኛ ጌታ በውኃ ላይ ሲሄድ 'መለኮት ስለሆንኩ ሄድኩ' አላለም። ጴጥሮስም በውኃ ላይ ሄዶአል። ውኃ ላይ መሄድ መለኮት አያሰኝም።

ፖዝ የሚነግረን ኢየሱስ 'ሰውየው ኢየሱስን' ነው። ሊያስተሰርይ ስለሚችለው ኃጢአት ሲያብራራ በበሽታ ምክንያት የመጣ ኃጢአትን እና ኃጢአታቸውን ይቅር ያላቿኋቸው ይቅር ይባልላቸዋል የተባለውን በማቅረብ። ከሐዋ. 2፥ 22 እና 36 በመጥቀስ ጌታ ሰው እንደነበረ ብቻ ከትንሣኤው በኋላ ግን ጌታና ክርስቶስ እንደሆነ አብራራ። ከልደቱ በፊት አምላክ፥ ከትንሣኤው በኋላ ሰውና አምላክ፥ በመካከል ግን (መሰይጠኑንም ሳንዘነጋ) ሰው ብቻ ነበር ነው የሚለን። ይህ የትውልድ መርዝ የሆነ ኢጋንንታዊ ትምህርት ነው።

ጌታ ኢየሱስ፥ 'መለኮት ስለሆንኩ ይህን አደረግሁ' እያለ መለከት እያስነፋ ምንም አለማድረጉን ወንጌላት ይነግሩናል። ኢየሱስን ሰው ብቻ የሚሉ እንደ ኢስላም ያሉ ሃይማኖቶች ትልቅ አድርገው የሚያቀርቡት ማስረጃ ይህ ነው። ጌታ ኢየሱስ እንዲያውም ማንነቱን ሰዎችም አጋንንትም ሲረዱ እንዳይገልጡ ይነግራቸው ነበር፤ ማቴ. 12፥15፤ ማር. 3፥12፤ 8፥30፤ ሉቃ. 9፥21-22፤ ወዘተ። ኢየሱስ እንዳይናገሩ የተከላከለው ሥጋ የለበሰ እግዚአብሔርን ስላልሆነ ሳይሆን የመጣበት ተልእኮ በመርሐ ግብሩ መፈጸም ስለነበረበት ነው።

> እኔ ዘላለም መለኮትን እንዴት ብለህ ስለምታምን ነው በምድር ላይ አልተጠቀመም ብለህ ያልከው? መለኮትን ገልጧል? ተአምራት መለኮት አይደለም። ተአምራት መሥራትሽ፥ የሆነ ነገር ማድረግሽ መለኮትነትሽን አያሳይም። . . . ለምሳሌ በምድር ላይ ሠላሳ ዓመት ሲመላለስ መለኮት

[5] እላይ የተጠቀሰው።

[6] እላይ የተጠቀሰው።



ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

ተገልጦበታል? ወይንስ መንፈስ ቅዱስ ተገልጦበታል? በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት በጥበብም በሞገስም ያድግ ነበር ነው የሚለው።

ከላይ ፖዝ ከተናገረው ውስጥ ያሰመርኳቸውን አሳቦች ስናጤን ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ እንደ ሰው ብቻ በመንፈስ ቅዱስ ቅባትና ኃይል የተመላለሰ ብቻ ነው። ይህ ወደ ምን እንደሚመራን ለመረዳት አይከብደንም። እኛም በመንፈስ ቅዱስ ቅባትና ኃይል ኢየሱስ እንደተመላለሰው መመላለስ፥ እንደሆነው መሆን፥ እንዳደረገው ማድረግ ይቻለናል ወደሚል ወደ ዘመናዊው የቃል-እምነት ትምህርት የሚወስደን ስሕተት ነው። ይህ ትምህርት ደግሞ በፖዝ አልተጀመረም፤ ይህንንን ስሕተት በማሰራጨትም እርሱ የመጨረሻው የዚህ መርዘኛ ትምህርት ደቀ መዝሙር አይሆንም።

ኢየሱስ ሰው ብቻ ሆኖ ኖሮ ሲጠመቅ ክርስቶስ ሆነ፤ ከአብ ድምጽ ሲመጣ ክርስቶስ ሆነ፤ በተራራው የአብ ድምጽ ሲመጣ ክርስቶስ ሆነ፤ በትንሣኤው ክርስቶስ ሆነ እያሉ ሊያስረዱ የሚሹ ከኒቅያ ጉባኤ ዘመን በፊት አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የቅባት እና የጸጋ ልጅ አስተማሪዎች፥ እስከ ዘመነኞቹ የቃል-እምነት አስተማሪዎች ድረስ አሉ። እግዚአብሔር የነበረው ቃል (ዮሐ. 1፥1) ሥጋ የሆነውና በእኛ ያደረው (ዮሐ. 1፥14) መለኮትነቱን ጥሎ ወይም ሽሮ አይደለም። በድንግል ማርያም ማኅጸን ከነበረበት፥ በቤተ ልሔም በረት እስከተኛው ሕጻን፥ በመስቀል ላይ እስከተሰቀለው ድረስ ኢየሱስ ሰው ብቻ አልነበረም።

ቤኒ ሂን ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ባይረዳው ኖሮ ኃጢአት ሊያደርግ የሚችል ሰው ብቻ ነበረ ይላል።[7] ሰው ብቻ። ይህንን የሚለው ሂን ብቻ ሳይሆን ብዙዎች የቃል-እምነት ሰባኪዎች ናቸው። በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደም የአንድ ተራ ሰው ብቻ ደም ነው። ሂን የሚለው ሲመላለስ ሰው ብቻ ሳይሆን በመስቀል ሰይጣን ሆኖ መሸነፉንና በሲዖል ድል ማድረጉንና ዳግም መወለዱንም ነው። ፖዝም የሚለን ይህንን ይመስላል። ኢየሱስ፥ 'እኔ አምላክ ስለሆንኩ ይህን አደረግሁ' እንዳላለ፥ 'እኔ ሰው ብቻ ስለሆንኩ ይህን አደረግሁ ወይም አላደረግሁም' አለማለቱን እግምት ውስጥ ሳያስገባ የራሱ ድምዳሜ ላይ ደርሶ ኢየሱስ ከጽንሰቱ እስከ ስቅለቱ ሰው ብቻ ነበረ፤ እንዲያውም ከሰውም የወረደና የሰየጠነ ነበረ ይለናል።

ኢየሱስ ሰው ብቻ ነበረ ማለት አንድ ባሕርይ ብቻ ነበረው ማለት ነው። መለኮታዊነት የሌለው ሰብዓዊ ብቻ የሆነ ነው ማለት ነው። ኢየሱስ አንድ ባሕርይ ብቻ ነው የሚሉ፥ ሰው ብቻ ነው የሚሉ፥ ሰውና አምላክ ተቀይጠ አንድ አዲስ ባሕርይ ተፈጥሮአል የሚሉ፥ አምላክነቱ ሰውነቱን ውጦት ተዋሕደው ተዋሕዶ ሆኖአል (እንደ ኢኦተቤ/ክ) የሚሉ፥ ሌሎችም በታሪክ ውስጥ የመጡና የሄዱ፥ እስከዛሬም ተጋቦታቸው ያልጠፉ ትምህርቶች ኖረዋል። ፖዝ የሚያቀነቅነው ይህ ከነአርዮስ ዘመን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን ሲያውክ የኖረና የታደሰ አሮጌ ኑፋቄ ነው። ግራ ቀኙን የማያውቀው የዋኅ መንጋ ባለማወቅ እየተጋተ ያለው መርዘኛ ትምህርት ነው።

> . . . <u>በምድር ላይ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ አልተመላለሰም።</u> አሁን በሰማይ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው። ዱሮ ወደ ምድር ሳይመጣ በፊት ፍጹም አምላክ ብቻ ነበር። በምድር ላይ ቤዛ ሲሆን በሰው ማንነት ሁለተኛው አዳም ሆነ። የአዳምን ቤዛነት በሚጨርስ ማንነት እራሱን ባዶ አድርጎ በምስሉ እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋርዶ ነው ሚለው። ጳውሎስ ነው ሚለው፤ የጳውሎስ መረዳት ነው ያለን።

ከዚህ የፖዝ የድፍረት ንግግር በግልጽ የምንረዳው ከመምጣቱ በፊት ፍጹም አምላክ፥ አሁን ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ እንደሆነ ሲሆን፥ በመካከል ግን መለኮትነት የሌለው ፍጹም ሰው ብቻ እንደነበር ነው። ክርስቶስን በየተለያዩ ዓመታቱ ገነጣጥሎ እንደተለያየ አድርጎ እንደሚያስተምር ለተጠየቀው ጥያቄ የመለሰው መልስ ይህንን ግልጽ ያደርገዋል፤

> . . . እስከ 30 ዓመቱ ማንኛውም ሰው የሚኖረውን ነው የኖረው፤ አናጢ ነበር ነው የሚለው፤ በቃ ኖርማል ነገር ነው። ከ30 ዓመቱ በኋላ ግን የጌታ መንፈስ በኔ ላይ ነው ብሎ የተቀባው መሢሕ አገለገለ ማለት ነው። ጌቴሴማኒ ጽዋውን ከጠጣ በኋላ ቤዛ ሊሆነን እያንዳንዷን የኃጢአተኛ ዋጋና ሥርዓት ከፈላት ማለት ነው፤ እስከ መስቀል። ከሙታን ሲነሣ የ30 ዓመቱ ኢየሱስ ነው? የ3 ዓመቱ አገልግሎት ነው? መስቀል ላይ ያለው ነው? አይደለም። አሁን በሌላ ክብር አይደል ምናውቀው? እስኪ ጳውሎስ ያለውን ጥቅስ ልጥቀስና ልጨርስልሽ፤ 2ቆሮ. 5 ማለት ነው፤ ክርስቶስን በሥጋ ያወቅነው ብንሆን እንኳ ከዚህ በኋላ እንደዚህ አናውቀውም ይላል። በሌላ መልክ እናውቀዋለን ማለት ነው። ስለዚህ መገነጣጠል ለምን አስፈለገ? እንግዲህ የሰነፍ አሳብ ነው።

የፖዝ ኢየሱስ በምድር ባገለገለበት ዘመን ሰው ብቻ (ሰውየው) ኢየሱስ ነው። ተወልዶ እስከሚሞት እንደ ሰው <u>ብቻ</u> ኖሮ ከሞት ሲነሣ ግን እንደገና አምላክና ሰው ሆነ። በሥጋው ወራት መለኮት ያልነካው፤ አማኑኤልነትን ያልተቀዳጀ፤ መንፈስ ቅዱስ እኛን እንደሚረዳን ብቻ የረዳው፤ ነፍሱ፥ ማዕበሉና ተፈጥሮ የታዘዘው በመለኮትነቱ ያልሆነ፥ 'እወዳለሁ ንጻ' ብሎ ያነጻው በመለኮት ያይደለ፥ ደካሞችን ወደራሱ የጠራ ወደ ሰውነቱ ብቻ የሆነ፥ የሰንበት ጌትነቱ የሰው ጌትነት ብቻ የሆነ፥ ቃል ተናግሮ በውኃ ላይ የሚያስኬድ የሰውነቱ ቃል ብቻ የሆነ፥ በፊታቸው ተለውጦ እንደ ፀሐይ የበራ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስነቱና የአይሁድ ንጉሥነቱ ሲጠየቅ እውነቱን የገለጠው ሰውየው ብቻ ኢየሱስ ነው ወይ?

ዮሐ. 1፥1-2 በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ይላል። ኋላ በቁ. 14 ይህ ቃል ሥጋ መሆኑ ተጽፎአል። ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። መጀመሪያ ቃል የነበረው ቃልን አውልቆ አስቀምጦ ነው ሥጋ የሆነው? ወይስ ቃል ራሱ ነው ሥጋ የሆነው። ጥያቄውን በሌላ መልክ ልበለው፤ ቃል ቃልነቱን ይዞ ነው ሥጋ የሆነው ወይስ ቃልነቱን ትቶ ነው ሥጋ የሆነው?

ትንሽ ዝቅ ብለን የምናየው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተነሡ በኢየሱስ ማንነት ላይ የተፈጠሩ የማንነት ጥያቄዎች አሉ። አንዳንዱ ኢየሱስን አምላክ ብቻ፥ ሌሎቹ ሰው ብቻ፥ ሌሎቹ ግማሽ አምላክና ግማሽ ሰው፥ ሌሎች ብዙው ክፍል አምላክና ጥቂት ሰው፥ ሌሎች ከሁለቱም ልዩ የሆነ ሦስተኛ አካል የያዘ ያደርጉታል። ሁለት ሰውና ሁለት ባሕርይ፥ አንድ ሰውና አንድ ባሕርይ የሚያደርጉትም አሉ። የኢየሱስ ማንነት ሰውም አምላክም በመሆኑ ልዩ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ኢየሱስ ሥጋ የለበሰ እግዚአብሔር ወልድ ነው። ያ የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነው ሥጋ የለበሰው። የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው እግዚአብሔር ሥጋ ለበሰ ማለት የሥላሴ ሁለተኛ አካልነቱን ደመሰሰ፥ ተወ፥ ከመሆን አቆመ፥ አውልቆ የነበረበት አስቀምጦ አምላክነቱ እዚያ ሰማይ፥ ሰውነቱ ደግሞ እዚህ ምድር ሁለት አካል ሆኖ ተመላለሰ ወይም ኖረ ማለት አይደለም። ኢየሱስ አንድ አካል ነው፤ በዚያ አንድ አካል ውስጥ ሁለት ባህርያት አሉ። ኢየሱስ በአንድ አካል ፍጹም ሰው እና ሙሉ አምላክ ሆኖ ተመላልሶአል። አንድ አካል ሁለት ባሕርያት።

ፖዝ የሚነግረን ኢየሱስ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ኢየሱስ ነው። ፖዝ ሊመልስልን የሚገባው የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ በሥጋ በተመላለሰባቸው 33 ዓመታት የት ነበር? ምን ያደርግ ነበር? ወይስ ይህ የሥላሴ ሁለተኛ አካልም ፖዝ ተደርጎ ነበር? እንደ ፖዝ ትምህርት እግዚአብሔር ወልድ ለ33 ዓመታት ከመለኮትነት ፖዝ የተደረገ ይመስላል።

[7] *Hinn, Benny;* Good Morning Holy Spirit, *Word Press, p.135-6, 1991.*

ይህ የክርስቶስ ሐዋርያ ዮሐንስ ያስጠነቀቀን ስሕተት ነው። ገና በዮሐንስ ዘመንም ይህ ችግር ነበረ። *ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።* ይላል። ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ እንደ መጣ፥ አምላክ ሥጋ ለብሶ ሰው እንደሆነ የማይታመን መንፈስ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው። ፖዝ የሚነግረን ኢየሱስ ግን በሥጋ የመጣው ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ ሳይሆን ሥጋ ወይም ሰው ብቻ የሆነ ኢየሱስ ነው። የተሰቀለው ኢየሱስ ያ ሰውየው ኢየሱስ ብቻ ነው።

ሐዋ. 2፥22ን እና 36 በማያያዝ ፖዝ ኢየሱስ የተሰቀለው ሰውየው ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ደግሞ ጌታና ክርስቶስ የተደረገው መሆኑን ሊያስረዳ ጥረት አድርጎአል። ይህ ሰው ዐውድ ስለሚባለው ነገር ፈጽሞ ግራ የገባው፥ ወይም ጨርሶ የማያውቅ፥ ወይም ሆን ብሎ ለማሳት ታጥቆ የተነሣ መሆኑን የሚያሳይ አጠቃቀስ ነው። ሐዋ. 2፥22 *የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤* ይላል። 'ሰው ነበረ' የሚለው ሐረግ ላይ ነው ያተኮረው። 36 ላይ ደግሞ፥ *እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።* ይላል። ከትንሣኤው በኋላ ጌታና ክርስቶስ ተደረገ።

በሐዋ. 2 ጴጥሮስ እየሰበከ ያለው ከአይሁድ ሦስት ታላላቅ በዓላት በዓለ ኀምሳ የተባለውን አንዱን ለማክበር ለመጡ፥ ምናልባት ፋሲካን አክብረው በዓለ ኀምሳንም ለመድገም እዚያው ለሰነበቱ አይሁድ ነው። ይህ ለክርስቲያኖች የቀረበ ስብከት አይደለም። በዚያን ወቅት ደቀ መዛሙርት ቁጥራቸው 120 ያህል ብቻ ሲሆን በዚህ ቀን ያልዳኑት ቀርተው የዳኑትና የተጠመቁት ብቻ እንኳ ሦስት ሺህ ነፍስ ነበሩ። እንግዲህ ይህ ስብከት ላልዳኑ አይሁድ የሰሰበከ ነው። "በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት" ብሎ በቀጥታ ነው የተናገረባቸውና፥ ምናልባት አብዛኞቹ ከኀምሳ ቀናት በፊት በነበረው ፋሲካ ቀን የተደረገውን ያዩና የተሣተፉ ናቸው።

እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ያውቁና ይረዱ የነበረው እንደ ሰው ብቻ ነበር። ስለዚህ፥ *ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤* ይላል እንጂ *ለእናንተ የተገለጠ አምላክ ነበረ፤* ሊል አይችልም። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ያዩት የነበረው እንደ ተራ ሰው ብቻ ነበርና። ኋላ ግን ጴጥሮስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ ሳይሆን ጌታና ክርስቶስ መሆኑን በመግለጥ፥ *ንስሐ ግቡ፥ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤* (ቁ. 38) ብሎ በስሙ እንዲጠመቁ ነበር ያዘዛቸው። ቀድሞ ጌታ ሰብከው ደቀ መዛሙርት ሲያደርጉ በአብ፥ በወልድ፥ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ነበር የነገራቸው። ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ ያዘዛቸውና የኃጢአታቸው ስርየት በስሙ ከመጠቃቸው ጋር የተቆራኘው ያልተቀበሉት ጌታ፥ ሰው ብቻ የመሰላቸውና ሰው ብቻ ያሉት ጌታ፥ እርሱ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን አምነው ቀድሞ የካዱትን አሁን ይቀበሉ ዘንድ ነው። ቢያውቁት ኖሮ ባልሰቀሉትም ነበራ!

የጌታ ሐዋርያ ጳውሎስ በ1ቆሮ. 2፥8 *ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፤* አለ። የክብርን ጌታ ነው የሰቀሉት። በመስቀል ላይ የተሰቀለው ጌታ ሰውየው ብቻ ኢየሱስ ሳይሆን የክብር ጌታ የሆነው ኢየሱስ ነው። ያላወቁትም እውነት ያ ነበር። ሰውየው ኢየሱስ ብቻ ነበር የመሰላቸው እንጂ የክብር ጌታ መሆኑን አላወቁም፤ ቢያውቁ ኖሮ ባልሰቀሉትም ነበር።

ጌታ ኢየሱስን አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉና ይሞክሩ የነበረው፥ ኋላም በእርግጥ የገደሉት በመካከላቸው የኖረና ያስተማረ ሰው ብቻ ወይም ሰውየው የሆነ አስተማሪ ስለነበረ አይደለም። ለምሳሌ፥ ዮሐ. 5፥18 *እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፦ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።* ይላል። በዚህ ጥቅስ ኢየሱስ ሁለት ነገሮች ማድረጉን እናስተውል። መጀመሪያ ሰንበትን ሻረ፤ ይህን ያደረገው የሰንበት ጌታ ስለሆነ ነው። ለአይሁድ ሰንበትን መሻር የሚያስገድል ኃጢአት ነው፤ ዘጸ. 31፥14፤ ዘኁ. 15፥32-36። ሁለተኛ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለ። መለኮትነቱን እዙፋኑ ላይ አስቀምጦ ብቻ ቢሆን የመጣው ይህ ማስተካከል ሊኖር አይችልም ነበር። ይህ መስተካከል ከትንሣኤው በኋላ የተነገረ ሳይሆን ከመስቀሉ በፊት የተገለጠ ነው። መለኮታዊ ሥልጣኑን ፈቅዶ አለመጠቀሙ፥ "ሰው ብቻ ነበር" አያሰኘውም። ለአይሁድ ኢየሱስ ማን መሆኑን መናገሩ ከቶም አልተድበሰበሰባቸውም። ሰው ብቻ ነኝ ያለ ሰው አይደለም እንዲሰቀል ያስደረጉት።

ጌታ ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ሲመረመር ሊቀ ካህናቱ ማንነቱን በጠየቀው፥ በተለይም የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ እርሱ መሆኑን በግልጥ በጠየቀው ጊዜ፥ ኢየሱስም፦ *እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ* ብሎ ተናገረ፤ ማር. 14፥62። ሊቀ ካህናቱ የቡሩክ ልጅ ያለው የሚጠብቁትን መሢሕ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ የሰው ልጅ ያለውም እርሱን ነው። ጌታ ራሱን፥ 'የሰው ልጅ' እያለ ይጠራ ነበር። ሰው ብቻ ስለሆነ አይደለም ራሱን የሰው ልጅ እያለ ይጠራ የነበረው። ይህ በደመና የሚመጣ የሰው ልጅ ለአይሁድ እንግዳ ቃል አይደለም። አይሁድ ይህ የሰው ልጅ ማን መሆኑን አሳምረው፥ አብጠርጥረው ያውቃሉ።

የሰው ልጅ የተሰኘው ሐረግ ለሰዎችም (ለምሳሌ ሕዝቅኤል ብዙ ተጠርቶበታል) ቢያገለግልም እዚህ ጥያቄ ላይ የቀረበው የሰው ልጅ ከዚህ በፊት የተነገረ ነገር ያለው የሰው ልጅ ነው። በዳን. 7፥13 *በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት።* ይላል። ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀድዶ ሌላ ምስክር አለማስፈለጉን መናገሩ የምናልባትና የግምት መረዳት አልነበረም። እዚህ ጌታ *የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ* ያለውና እዚያ በዳንኤል *ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤* የተባለው አንድ መሆናቸውን የአይሁድ አለቆች አሳምረው ያውቃሉ። ለነዚህ የአይሁድ አለቆችና ካህናት መልስ ይሰጥ የነበረው ኢየሱስ ሰውየው ኢየሱስ ብቻ አልነበረም።

በመስቀል ላይ የተሰቃየውና የሞተው ጌታ 'ሰው ብቻ' የሆነው ኢየሱስ አልነበረም። እርግጥ ነው መለኮት እንደማይሞት የታወቀ ነው። 'ሰው ብቻ' ግን፥ ቢበዛ የራሱ ቤዛ ነው የሚሆን እንጂ ስለሌላው ቤዛ ሊሆን አይችልም። ስለ ሌላ ቤዛ የሚሆነው፥ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት የሚያስወግደው ሰው፥ 'ሰው ብቻ' አልነበረም። ይህ ሰው ከሰው ብቻነት ከአዳምነት ያለፈ ነው። አምላክ መለኮቱ ሳይሰረዝ ሰው፥ ቃልም ቃልነቱ ሳይጠፋ ሥጋ የሆነው ለዚህ ነው። ተራ ሰው የኔን የአንዱን ሰው ኃጢአት ብቻ እንኳ መሸከም አይችልም። ይህ ሰው ተራ ሰው ሳይሆን **አምላክ ሰው** (በስነ መለኮት ቋንቋ ቴአንትሮፖስ) ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተደረጉት ትልልቅ ጉባኤዎች በኢየሱስ ማንነት ላይ የተከራከሩና ያረጋገጡ ጉባኤዎች ነበሩ። በኬልቄዶን በ325 ዓ. ም. የተደረገው በአርዮስ ትምህርት ላይ፤ 381 ዓ. ም. በቁስጥንጥንያ የተደረገው በአርዮስ፥ በአቡልናርዮስ፥ እና በሰባልዮስ ትምህርት ላይ፤ በ431 ዓ. ም. በኤፌሶን የተደረገው በንስጥሮስ፥ በጳላግዮስ እና በእመአምላክነት ጉዳይ ላይ፤ በኬልቄዶን በ451 የተደረገው በአውጣኪ እና በኢየሱስ መለኮትና ስብዕና ላይ


ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥
የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

(ይህ 4ኛው ጉባኤ አውጣኪና የአንድ ባሕርይ ትምህርቱ በአገራችን ተዋሕዶ የሚባለው የተወገዘበት ትምህርት ነው)። እንዲህ እያልኩ ቀጣዮቹን ጉባኤዎችም መዘርዘር ይቻላል። ነጥቤ፥ እነዚህ ጉባኤዎች ስለተቀመጡና ተነጋግረው እምነታቸውን ስለገለጡ ወይም ስሕተትን ስላወገዙ ብቻ ትክክል ናቸው ማለት ሳይሆን የተነጋገሩባቸው የቃሉ እውነቶችና ያወገዟቸው የተሳሳቱ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ወይ ማለት አግባብ መሆኑና እነዚህ ስሕተቶች እንዳልኖሩ መቁጠር ስሕተት መሆኑን ነው።

የኒቅያ ጉባኤ የተቀመጠው አርዮስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተለየ ማንነት ስላለው ነው ብሎ ያስተማረው ትምህርት ስለናኘ ነበር። ዘመናዊዎቹ አርዮሳውያን የይሖዋ ተከታዮች ይህንን ነው የሚያስተምሩት። ንስጥሮስ የተባለው ኢየሱስ ሰው ብቻ ሆኖ ነገር ግን በአምላክ ቃል (ሎጎስ) ይደገፍና ኃይል ያገኝ ነበር ይላል። አውጣኪ የተባለው ክርስቶስ ሰውም አምላክም ያይደለ ሦስተኛ ሌላ (በሮማይስጥ tertium quid) ነው ብሎ ነበር። ይህን ተከትሎ ሞኖፊሳይቶች (አንድ ባሕርይዎች) መለኮታዊው ባሕርይ ሰብዓዊውን ሰልቅጦታል የሚል ትምህርት ገነነ። እንዲህ እያሉ የክርስቶስን መለኮትና ሰብዕና በተመለከተ የተፈጠሩትን ስሕተቶች ሁሉ ለመዘርዘር ብዙ ናቸው። ሰውየው ኢየሱስ ለፖዝ የተገለጠ አዲስ ስሕተት አይደለም።

በአገራችንም እንኳ በኛ ቆጠራ በ1870 ዓ. ም. በቦሩ ሜዳ የተደረገው ጉባኤ በክርስቶስ ማንነት ላይ ነበረ። ቀድሞ ቅባት፥ ካራ፥ ተዋሕዶ፥ እና የጸጋ ልጅ የተባሉ በክርስቶስ ማንነት ላይ የነበሩ የቆዩ የተለያዩ ትምህርቶች ነበሩ። ወደነዚህ ሁሉ በዝርዝር መግባት ራሱን የቻለ ሥራ ነው። ግን የቀደሙትም ሆኑ የአገራችን ጉባኤዎች እዚህ ሰየጠነ፥ ሰው ብቻ ነው፥ ፖዝ የሚያደርግ ሰው ሾመ በተባለው ኢየሱስ ላይ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። የፖዝ አቋም ኢየሱስ ከጽንሰቱ እስከ ትንሣኤው ሰይጣንነትንም ጨምሮ፥ ሰው ብቻ ነው እንጂ ምንም መለኮትነት የለውም የሚል ነው።

ፖዝ ጌታ ኢየሱስ ስግደት ሲቀበል ለነገሥታት እንደሚቀርብ ያለ ስግደት ብቻ ነው የተቀበለው እንጂ ለአምላክ የሚቀርብ አምልኮ አልተቀበለም ይላል። እርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ስግደቶች ሁሉ የአምልኮ አይደሉም። አንዳንዱ ስግደት የአክብሮትና የሰላምታ ስግደት ሊሆን ይችላል። ግን አንዳንዱ የአምልኮ ስግደት ነው። ገና ሕጻን ሳለ የሰገል ሰዎች አልሰገዱለትም? (ማቴ. 2፥2-11) ሰግደውለታል። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ሰላም ሊሉት አይደለም የመጡት። ይህ ስግደት የሰላምታ ስግደት አይደለም። እዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለው ስግደትና በሌሎች ቦታዎች፥ ለምሳሌ፥ ማቴ. 4፥9-10 ሰይጣን ጌታን እንዲሰግድለት የጠየቀው ቃል ተመሳሳይ ነው። ሰይጣን ጌታን፥ 'ሰላም በለኝና ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ' እንዳላለው መቼም ግልጽ ነው። በግልጽ ጌታም ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሚሰገድ የተጻፈውን ጠቅሶ እዚያው ተናግሮአል። ይህ ቃል አምልኮ ነው። በማቴ. 14፥32 የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው የሰገዱለት ከማንነቱ ጋር የተቆራኘ አምልኮ ነው። የአምልኮ ስግደት ደግሞ ለአምላክ ብቻ የሚሰጥ ነው።

ጌታ ይቅርታ ሲያደርግና ኃጢአት ሲያስተሰርይ ማንም ሰው የሚያደርገውን ዓይነት ስርየት ብቻ ነው ያደረገው እንጂ ከአምላክ በቀር ማንም ሊያደርግ የማይችለውን ስርየት አላደረገም ይለናል ፖዝ። ተአምራት ሲያደርግም ተራ ሰው የሚያደርገውን ተአምር ብቻ ነው ያደረገው ነው የሚለን። የሚደንቅ ድፍረት ነው! ፖዝ በኢየሱስ አገልግሎት ልክ የሆነ ተአምራት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ስግደት መቀበልና ስርየት መስጠትም እንደሚችል ነው የተናገረው። መጥተው እግሩ ስር የሚወድቁ ሰዎችን፥ 'እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ነው የምላቸው' ይላል። ከጌታ የተበደረው ቋንቋ ነው። ቶሎ ካልመለሰው ብዙ የሚወልድበት ብድር ነው።

ጌታ ክርስቶስ ኃጢአትን ሲያስተሰርይ ወይም ይቅር ሲል፥ ጻፎችና ፈሪሳውያንም፦ ይህ የሚሳደብ ማን ነው? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው ያስቡ ጀመር። ተብሎ ተጽፎአል፤ ሉቃ. 5፥21። መረዳታቸው ግልጽ ነው። ጌታም መረዳታችው ስሕተት ቢሆን ኖሮ ባረመ ነበር፤ ነገር ግን የጌታ መልስ ግልጽ ሆኖ፥ ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአት ሊያስተሰርይ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ብሎ፥ ሽባውን፦ አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥ አልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው። ነበር፤ ቁ. 24። ኢየሱስ እንደ ሰውነቱ ሥልጣኑን ሁሉ ባይገልጥም እዚህ የሰው ልጅ ሥልጣንና የእግዚአብሔር ሥልጣን ተስተካክለው ነው የታዩት።

በጌታ ሕይወት ሰብዕናውንና መለኮትነቱን ተጣምረው የምናይባቸው ቦታዎች በርካታ ናቸው፤ ለምሣሌ፥ አልዓዛርን ከማስነሣቱ በፊት እንደ ሰውነቱ አነባ፤ ግን እንደ አምላክነቱ ከሙታን ጠርቶ አስነሣው፤ ዮሐ. 11። በታንኳዋ ውስጥ እንደ ሰውነቱ ደክሞት ተኛ፤ ተነሥቶ ግን እንደ አምላክነቱ ባሕሩንና ማዕበሉን ዝምና ጸጥ እንዲሉ ተናገራቸው፤ ማር. 4። የእግዚአብሔርና የሰው በክርስቶስ አንድ መሆን ታላቅ ድንቅ ነገር ነው። ሙሉ በሙሉ ባይገባን ሊያስገርም አይገባም። ስላልገባንም የሆነውን ኹነት ልንክድ የተገባ አይደለም። ወይም እስከገባን እስከ ዝቅተኛው ደረጃ ልናወርደው ለመሞከር እኛ ራሳችን የተገባን አይደለንም።

በቃለ መጠይቁ መካከል ስለ ኢየሱስ ሰው ብቻ ስላለመሆኑ መለኮት ከመሆኑ ጋር ስለመታጀብ ተነሥቶ ሲጠየቅ፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሊወግሩት ሲሉ በመሃላቸው አልፎ ሄደ ሲል እኮ ዝም ብሎ አልፎ ሄደ እኮ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ በመሃላቸው አልፎ ሲሄድ መለኮታዊ መሰወር አለ፤ ጠፋባቸው።" ካለ በኋላ፥ ኢየሱስ ስለመሰወሩ በመናገሩና ያንን መሰወር 'መለኮታዊ መሰወር' በማለቱ (አምልጦት መሆን አለበት)፥ በጋዜጠኛዋ ታዲያ ያ መለኮታዊ ማንነቱን አያሳይ እንደሆነ ሲጠየቅ፥ "ይሰወራል የሚለው ቃል እኮ የመለኮት መለኪያ አይደለም ብዬ ነግሬሻለሁ። መሰወር የሚለው ቃል፥ ጠንቋይስ ይሰወር የለ እንዴ አንቺ? ምን፥ ከባድ ነው መሰወር? ተሰውረው ይሄዳሉ እኮ? ይበርራሉ በአየር ላይ።" ብሎ ነበር።

ኢየሱስ ምንም መለኮታዊነትን አለመግለጡን፥ እንዲያውም ከዓለማችን ጠንቋዮች የተለየ ሥራ አለመሥራቱን፥ ሰው ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገ የተነወረና አሳፋሪ ሙከራ ነው። አሳፋሪ ያልኩት፥ 'መለኮታዊ መሰወር' ብሎ ተሳስቶ ከተናገረ በኋላ መልሶ የተፋውን መዋጥ በመገደዱ ነው። ስነ መለኮቱ ገና ተቀርጾ ያላለቀ ስለሆነ ይሆናል እያመለጠውና እየተሳሳተ ኋላ የሚያርመውን ነገር የሚናገረው። በዚሁ በመጨረሻ ወደተነሣው ወደ ታጃቢው ኢየሱስ እንለፍ።

# 4. ታጃቢው ኢየሱስ?

**ኢየሱስ በአጃቢዎች እየተከበበ ይመላለስ ነበር!** ይህ በመግቢያው ላይ እንዳልኩት መነሣት ያለበት ከባድ ጉዳይ ሆኖ አይደለም፤ ግን ይህም በኢየሱስ ላይ የተቃጣ ዘለፋ ስለሆነ ብቻ ነው የማነሣው፤ ብዙ አልልበትም። ፖዝ አንድ ስፍራ ላይ ሊናገር እንደሞከረው ይህ የመታጀብ ጉዳይ እርሱ ያስደረገው ሳይሆን ሌሎች ያደረጉት ነገር መሆኑን በአጭሩ ገልጦ አላስፈላጊ ዝባዝንኬነቱን ተናግሮ ሊያልፍ ሲችል እየሞገተ ትክክል መሆኑን መናገሩና ታጅቦ መሄዱን ለማጽደቅ ወይም ትክክል መሆኑን ለማሳየት ምሳሌ አድርጎ ኢየሱስን በመጥቀሱ ነው ልናገርበት የምፈልገው።

በአጃቢ መሄዱን ሲገልጥና ትክክልነቱን ሲያስረግጥ፥

> *መጀመሪያ በጋርድ የሄድኩት እኔ ነኝ። ሁሉ ነገር ስፍራ አለው፤ እስታንዳርድ አለው፤ ደረጃ አለው፤ አሠራር አለው። . . . በጋርድ መሄድ*

> ምንድነው ፐርፐዙ? ዓላማው ምንድነው? ደግሞስ ሲቀጥል፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ? ጌታ ኢየሱስጋ ሰዎች ሕጻናት ልጆች ይዘው መጡ ይላል። ደቀ መዛሙርቱ ከለከሏቸው ይላል። ጌታ ኢየሱስ አትከልክሏቸው አለ ይላል። በሌላ አማርኛ ጌታ ኢየሱስጋ ማንም ሰው ከመድረሱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ይከለክሉ ነበር ማለት ነው። . . . ሉቃስ የሚለው ፊልም ላይ አይተሻል? ጅራፍ ይዞ ገርፎ አስወጣቸው፤ ከዚያ በኋላ ሰዎች ተበጣበጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ከለሉት። ፊልሙ ላይ ያየሁትን ነው ምነግርሽ። . . . ሪያሊቲው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ፖዝ ፊልምን እንደ ምስክር መጥቀሱ እጅግ በጣሙን ቢያሳፍርም (የትምህርቱ ምንጭ ፊልምና የቴሌቪዥን ሰባኪዎች ይሆኑ?)፥ ስለ ፕሮቶኮልም ተናግሮአል። በስነ ሥርዓት እና የመስተንግዶ አገልግሎት ላይ ማንም ጥያቄ የሚያነሣ ሰው የሚኖር አይመስለኝም። ነገር ግን ጋዜጠኛዋም በግልጽ ያነሣችው የአስተናጋጆችን አገልግሎት ሳይሆን የዘብ አጀብ (security detail) ተግባር ነው። የምመከተው ጉዳይ ስለ ጌታ የተነገረውን በመሆኑ እዚህ ላይ ብቻ ላተኩር እወዳለሁ።

ፖዝ ኢየሱስ ታጅቦ ይሄድ እንደነበር ዋና ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው ሐዋርያቱ ሕጻናትን መከልከላቸውን ነው። ይህን ክፍል ሳያነብብ ሲጠቅስ ልክ እንደተጻፈ አስመስሎ ነው የተናገረው። 'ደቀ መዛሙርቱ ከለከሏቸው' ብሎ ነው የተናገረው። ይህ ያዘመሙ ዘመነኛ 'ሐዋርያት' ከቅዱስ ቃሉ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና የአጠቃቀስ ዘይቤ የሚያሳየን እውነት ነው። ያልተጻፈ ቃል እንደተጻፈ ተደርጎ ሲነገር ቃሉን ያላነበቡ ተመልካቾች ወይም አድማጮችም እውነትም የተጻፈ ይመስላቸዋል። እዚህ ሐዋርያቱ የከለከሏቸው ሊመስላቸው ይችላል።

ይህ ታሪክ በሦስቱ ወንጌላት (ማቴ. 19፤ ማር. 10፤ እና ሉቃ 18) ተጽፎአል። ፖዝ የሚያስተዋውቀንን ኢየሱስ ማንነት ለማጨፍገግ ከመስመር ለመውጣት ደስተኛ ስለሚሆንና ቃሉን የራሱን ፍላጎት መፈጸሚያ ለማድረግ ከአሳቾች እንደ አንዱ ስለሚጠቅስ ነው ይህን ቃል መጥቀስ ያስፈለገኝ። በሦስቱም ወንጌላት እነዚህ ክፍሎች ሕጻናትን እንዲዳስሳቸው ወደ እርሱ ማምጣታቸውን፥ ሕጻናቱም ኢየሱስ ዘንድ መድረሳቸውን እንጂ ለማምጣት ከአጋፋሪዎች ጋር ግብግብ መግጠማቸውን አይናገሩም።

ማቴዎስ፤ በዚያን ጊዜ እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ገሠጹአቸው።

ማርቆስ፤ እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው።

ሉቃስ፤ እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን ደግሞ ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም አይተው ገሠጹአቸው።

በሦስቱም ወንጌላት ሕጻናቱ ወደ ኢየሱስ መጥተዋል። ወደ ኢየሱስ ደርሰዋል። ካመጡ በኋላ ነው ደቀ መዛሙርቱ ያመጧቸውን ሰዎች የገሠጹት እንጂ ሳያመጡ ከሩቅ አላገዷቸውም። ኢየሱስን እንደ ክብር ዘብ ሆነው አልከለሉትም። ቢሆንማ ኖሮ ያመጧቸው ተግሣጽ ለመቀበል ወይም ኢየሱስም ሕጻናቱን ለመባረክ ዕድሉ ባልኖረም ነበር።

ዛሬ በአጃቢ የሚሄዱ ሐዋርያትና ነቢያት ተብዬዎች መኖራቸው አያስደንቅም። "መጀመሪያ በጋርድ የሄድኩት እኔ ነኝ፤ . . . በቢልቦርድ መጀመሪያ የወጣሁት እኔ ነኝ . . ." ማለቱ ለማንነቱ የሚሰጠውን ስፍራ ይገልጠዋል እንጂ ፖዝ የመጀመሪያው ታጃቢ አልነበረም፤ የመጨረሻውም አይሆንም። እነዚህ ሰዎች እኮ የሚኮርጁት ኢየሱስንና የመጀመሪያዎቹን ሐዋርያት ሳይሆን ርእሳነ ብሔሮችን፥ ቱባ የክልልና የግዛት ባለ ሥልጣናትንና የትልልቅ ኮርፖሬሽን ዲሬክተሮችን ነው። ይህ የሚያሳየን ከአለባበስ እስከ አኗኗር ድረስ ሞዴሎቻቸው ዓለማውያን መሆናቸውን፥ ከመደዴው ክርስቲያን ተርታ የወጡ ጥዩፎች መሆናቸውን ነው። በዚህ ዘመን የዓለምን መንግሥታትና ክብራቸው አይተው የወደቁና የሰገዱ 'ሐዋርያት' ተብዬዎች በዝተዋል። አሳጃቢዎችና አጃቢዎች እስካሉ ድረስ ታጃቢዎች ደግሞ ይኖራሉ። ለምጽፈው ነገር ማየት ስለኖረብኝ አንድ ሁለቱን ሐዋርያና ነቢይ የተባሉ ታጃቢ ሹሞች እየቀፈፈኝ አይቻለሁ። ሁለቱም ጅንኑዎችና ኩራታቸው አናታቸውን በርቅሶ የወጣ ይመስላሉ። አረማመዱንም ጭምር አስቀድሞ የተለማመዱት ይመስላሉ። ማየቱ ራሱ አሳፋሪ ነው።

እነዚህን ትተን ወደ ኢየሱስና ወደ ደጎቹ ሐዋርያት እንመለስ። ኢየሱስ በአጋፋሪዎችና አንጋቾች የሚታጀብ ቢሆን ኖሮ ያቺ 12 ዓመት ደም ሲፈስሳት የኖረች ደካማ ሴት ልብሱን ትዳስስ ነበር? ጌታ የዳሰሰው ማን እንደሆነ ሲጠይቅ ደቀ መዛሙርቱ የመለሱት መልስ፥ *ሕዝቡ ሲያጋፉህ እያየህ፡- ማን ዳሰሰኝ ትላለህን?* ነበር። ሕዝቡ ሲያጋፉህ እያየህ! ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላው እንዲጋርዳቸው ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው ያኖሩ ነበር፤ ሐዋ. 5። ጴጥሮስ በአንጋቾች አልታጀበም። ከጳውሎስ ከአካሉ ጨርቅ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር፤ ሐዋ. 19። 'ከአካሉ' የሚለው ከለበሰው ልብስ፥ ከላዩ እየተቆረጠ መሆኑን የሚያሳይ አገላለጥ ነው። ከላዩ በካራ እየቆረጡ ሲወስዱ አጃቢ ከልካይ አልነበረም። እንኳን ሌላ እርሱም ራሱ የተከላከለ አይመስልም። አጃቢ፥ አጋፋሪ፥ ከልካይ፥ ተከላካይ የለም። ይህ ከተርታው ክርስቲያን ወገኖቻቸው ጋር እንደ ወንድሞች መደባለቃቸው ውበታቸውም ነበር።

ከላይ እንዳልኩት ይህ የአጀብ ግርግርና የትኩረት ጥማት እንጂ አስተምህሮታዊ ጉዳይ ስላልሆነ ትልቅ ችግር መሆን የለበትም። ሐዋርያ ፖዝ እና ዘበናይ ሐዋርያት በአጀብ ቢሄዱ፥ ግምጃ ይነጠፍልን፥ ሳር ይነስነስልን፥ ቄጠማ ይጎዝጎዝልን፥ ማንም አይንካን፥ ከላይ ፀሐይ፥ ከጎን የሰው ዓይን አይውጋን፤ ጋርዱን፥ ከልሉን፥ ከደኑን፥ ሸፍኑን ቢሉ አያስደንቅም። የሚያስደንቀው እና ይልቁንም የሚያሳፍረው ግን ኢየሱስንና የኢየሱስን ሐዋርያት የዚህ ስንፍናቸው ምስክር አድርገው ሲጠሩ ነው። ኢየሱስ ታጃቢ አልነበረም። የክርስቶስ ሐዋርያትም የኢየሱስ አጃቢዎች አልነበሩም። እንዲያውም በቀውጢዋ ሰዓት ጥለውት ነበር የሸሹት። ጌታ ብዙ ጭፍራ የመላእክት ሠራዊት እንዲከላከሉለት ማድረግ እየቻለም አላደረገም። ጌታ አማኑኤል ነበረ፤ እግዚአብሔር ከሰው ጋር። ጸጋና እውነትን ተመልቶ በሰዎች ያደረ ጌታ ነበረ። ኢየሱስ፥ 'ወደ እኔ ኑ' ብሎ የጋበዘ ጋባዥ ነበረ። ኑ ሲል ብረት ለበስ ታጣቂዎች አቁሞ አልነበረም። ኢየሱስ ታጃቢ አልነበረም።

# መደምደሚያ

**መሆንና ማድረግ።** የሐዋርያ ፖዝ ስሕተት ዋና አደጋ ኢየሱስ ሰው ብቻ ሆኖ ስለተመላለሰ እርሱ የሆነውን **እንሆናለን** ወይም ያደረገውን **እናደርጋለን** የሚል ነው። የሆነውን መሆን እንደማንችል በግልጽ የታወቀ ነው። እኛ በእግዚአብሔር ጸጋና መንፈስ ዳግም ተወለድን እንጂ በባህርያችን ኃጢአተኞች ሆነን የተወለድን ሰዎች ብቻ ነን እንጂ መለኮት አይደለንም። ከመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር የተነሣ የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች ተደረግን እንጂ ምንም መለኮትነት የሌለብን ሌጣ ሰዎች ብቻ ነን፤ ያውም ኃጢአተኞች።

እዚህ ላይ መስመር መሰመር አለበት። ኢየሱስ አምላክነቱን ሳይጥል ሰው እንደመሆኑ እኛ ሰውነታችንን ይዘን ወይም ጥለን መለኮት እንሆናለን ማለት የሐሰት ትምህርት ነው። ይህ ትምህርት ግን አዲስ አይደለም፤ ዛሬም በቃል-እምነት ትምህርቶች ዙሪያ የሚደመጥ ነው። በአገራችንም፥ 'መንፈስ ነን' ከሚሉቱ ጀምሮ፥ 'አንሞትም፥ እርሱ እንደሆነው ነን፥ እንዳደረገው እናደርጋለን' እስከሚሉቱ የሚታይ ስሕተትም ነው።

ወደ ኢየሱስ ማንነት ስንመጣ ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ እንደ ሰው ብቻ ተመላለሰ፤ ይቅርታ ያደረገው እኛም የምናደርገውን ነው፤


ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2016
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

ተአምራቱም እኛም የምናደርጋቸው ናቸው . . . የምንል ከሆነ ሌሎቹንም በመለኮቱ ብቻ በምድር ያደረጋቸውን ነገሮች በመሆንና በማድረግ ልናሳይ ልንገደድ ነው። በመጀመሪያ ራሳችንን፥ 'አምላክ ነን' ብለን መቀበል አለብን። ጌታ ኢየሱስ አምላክ የሆነውን ማንነቱ አውልቆ አንድ ስፍራ ደብቆ አስቀምጦ በሰውነቱ ስብዕና ብቻ አልተመላለሰም። አማልክት ነን የሚል ትምህርት አዲስ አይደለም፤ ደግሞም የብዙ ሃይማኖቶች ትምህርትም ነው። በክርስትናም ጥቂት ጥቅሶችን ከዐውዳቸው፥ ከአካላቸው ነቅለው ሰዎችን አማልክት ሊያደርጉ የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ። ጌታ ግን በሚያገለግልበትና በሚያስተምርበት ጊዜ ማንነቱን አልደበቀም። አይሁድ ሲከስሱትና እንዲሰቀል ሲያደርጉት ሰው ብቻ መሆኑን ተናግሮ ከመሰቀል በተረፈም ነበር። አይሁድ ሊወግሩት የሞከሩት፥ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን የቀደደው ስር ነቀል ትምህርት ያስተማረ ሰው ብቻ ስለሆነ አይደለም።

እንደ ኢየሱስ ነን ካልን አምልኮን ለመቀበል ሥልጣን አለን ማለት ነው፤ ኢየሱስ ይህን ከትንሣኤው በኋላ ብቻ ሳይሆን በፊትም ተቀብሎ ነበርና፤ ማቴ. 14፥32-33፤ ዕብ. 1፥6። የዘላለም ሕይወትን ማደል ይቻለናል ማለት ነው፤ ዮሐ. 10፥27-28። በሥልጣናችን ኃጢአትን ማስተስረይ ይቻለናል፤ ማር. 2፥5-11። የፈሰሰው ደም የፍጹም ሰው ብቻ ደም ነው ልንል ነው፤ ሐዋ. 20፥28። እንደ እግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ያለው ቃል መናገር እንችላለን ማለት ነው፤ ማቴ. 5፥27-29። እንዲህ እያልን መዘርዘርና መቀጠል እንችላለን። ፖዝ ከንግግሩ እንደምንረዳው እነዚህን ነገሮች መሆንና ማድረግ እንደሚችል ያስብ ይሆናል። ይቅርታ ማድረግን ኃጢአትን ከማስተስረይ ጋር አመሳቅሎ ማመሳሰል ራስን ወደ አምላክ ሥልጣንና ማንነት ማስጠጋት ነው።

**ተአምራት ማድረግስ?** የሆነውን አለመሆናችን በብዙዎች በአክብሮት እንደሚታሰብ፥ የሚያደርገውን እናደርጋለን የሚለውን ግን ጠንቀቅ ብለን እንድናየው ያስፈልጋል። በጌታ ስም ተአምራት እንደሚደረጉ የታወቀ ነው። ግን ተአምራት ሁሉ ሲደረጉ በጌታ ብቻ እንደተደረጉ ካሰብን የማንወጣበት፥ ከወጣንም ተጋግጠን የምንወጣበት ወጥመድ ውስጥ እንገባለን። ሰይጣንም ተአምራትን ሊሠራ ይችላል፤ የሚያምኑትን እንኳ እስኪያስት ድረስ መሥራት ይችላል። ዛሬ አፍ የሚያስከፍቱና የሚያስጨበጭቡ፥ ግን መንፈሳዊ ሕይወትን ከመሬት ግማሽ ክንድ እንኳ ከፍ የማያደርጉ ምልክቶች እየሰማንና ውሸታም ተአምራትን እያየን ነን።

'ጌታ በምድር ሲመላለስ ያደረጋቸውን ተአምራት እናደርጋለን፤ ማድረጋችንም እንደ እርሱ የመሆናችን አስተማማኝ ማረጋገጫ ነው' ከተባለና ምልክቶቹ ሁሉ ቢደረጉ ምልክቶቹ የዚያ ሰው ኢየሱስን በትክክል መምሰል ዋና አረጋጋጭ ሊሆን ነው ማለት ነው። ስሕተት! 'የተአምራቱ ምንጭ ማን ነው?' ነው ጥያቄው። ዛሬ እየሆነ ያለው ነገር ቤተ ክርስቲያን በተባለ ቦታ የሚደረጉ ድንቆች ሁሉ ወይም በኢየሱስ ስም የተደረጉ ነገሮች ሁሉ በጌታ የተደረጉ ተአምራት ናቸው ብሎ በየዋኅነት የመቀበል ስሕተት ነው። ይህ ተአምራትን ማፈንፈን በአሳቹ ጠላት ፉርጎ ውስጥ በጅምላ ለመነዳት መሳፈር ነው። ለመጋለብም ጀርባን መስጠት ነው።

ተአምራት ሲደረጉ እንዲያው አፍ ከፍቶ በመደነቅ ፈንታ መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄዎች አሉ። ጥቂቶቹ፤

1. ተአምራቱ ምን ፈየዱ? ውጤታቸው ምን ሆነ? የአያትህ ስም፥ ወይም ቀን የበላሸው ምሳ፥ ወይም ኪስህ ውስጥ ያለው ጫት፥ ወይም ፍሪጅሽ ውስጥ ያለው መድኃኒት መነገሩ ጥንቆላ እንጂ ተአምር አይደለም። ተአምራት የተፈጥሮ ሕጎች በገሃድ ሲጣሱ ነው። ሰማይ ሲዘጋና ሲከፈት፥ ውኃ ወደ ወይን ሲቀየር፥ የሞተ ሲነሣ፥ ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ ወደ 15 ሺህ ሰው አጥግቦ ሲተርፍ ነው። የተፈጥሮ ሕግጋት ተለጉመው ተይዘው እግዚአብሔር የከበረበትና የሰዎች ሕይወት የተሠራበት ተአምር ተደረገ ወይስ የምልክቶች ርችት ተተኮሰ?

2. ተአምራቱን አድራጊው ሰው ትምህርቱና ሕይወቱ ክርስቶስን ይመስላል? ክርስቶስ ምን ይመስል ነበር? ጌታ ምን ይመስል እንደነበር አራቱ ወንጌላት ይናገራሉ። ደግሞስ፥ ኑሮአቸውና ምስክርነታቸው የቀደሙትን ሐዋርያት ይመስል ነበር? የቀደሙት ሐዋርያት ትምህርትና ኑሮ ምን ይመስል እንደነበር ከሐዋርያት ሥራና ከመልእክቶቻቸው እናነብባለን። ያንን የማይመስል ከሆነ የክርስቶስ ሳይሆኑ የራሳቸው ሰዎች የመሆናቸው ዋና አመልካች ነው። እንግዲህ ተአምራት በሚደረጉባቸው ቦታዎችና ጊዜዎች ከሆንን ከተአምራቱ ይበልጥ ማየት ያለብን ሰዎቹ ናቸው። ሰዎቹ በኑሮና በሕይወት ያልተገለጡና ምስጢራውያን ከሆኑ፥ ትምህርታቸው የደፈረሰና ያልጠራ ከሆነ ልንጠረጥር ይገባናል።

3. ምልክቶችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ናቸው ብለን መቀበል ስሕተት ነው። ሰይጣንም ምልክቶችን ሊያደርግ እንደሚችል መታወቅ ሊቅነትን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆን የለበትም። ማቴ. 7፥22-23 በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ። ይላል። በዚህ የምናየው በስሙ ትንቢት የተናገሩ፥ አጋንንት ያወጡ፥ ተአምራት ያደረጉ፥ ተአምራት ብቻ ሳይሆን ብዙ ተአምራት ያደረጉ፥ ግን ከቶ ያልታወቁ የነበሩ ሰዎችን ነው። ልብ እንበል፤ እነዚህ ነገሮች የተደረጉት በጌታ ስም ነው። ነገሮቹ በእርግጥ ተደርገዋል። በሰይጣን ሳይሆን በጌታ ነው የተደረጉት። ነገሮቹ የተደረጉት ከአድራጊዎቹ ማንነት የተነሣ ሳይሆን፥ እነርሱ ማንም ካለመሆናቸውና ከጌታ ማን መሆን የተነሣ ነው።

እነዚህን ከላይ የጠቀስኳቸውን ሦስት ነጥቦች እንደ መደምደሚያ ላነሣ የወደድኩት ጌታ የሆነውን ሆኖና ያደረገውን አድርጎ ማንነትን ማሳየት የጠቅላላው ጽሑፍ ዘለላ አሳብ ስለሆነ ነው። ዛሬ ክርስቲያኖች ምልክታሞች፥ ምልክት አፈንፋኞች እንዲሆኑ ዘመቻ እየተደረገ ያለ ይመስላል። ምክንያቱም ስለ ክርስቶስ ማንነት ከሚያውቁት ይልቅ የሚደረጉት ትዕይንቶች የሚሰበስቡት አፍ ከፋች አድናቂ ሕዝብ ቁጥር እጅግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮቶች የከበረ ስፍራ በሰው ሠራሽና በአጋንንታዊ ትምህርቶች እንዳይለወጡ ትጉሃን የቃሉ ተማሪዎች ልንሆን ይገባናል። ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፤ ማቴ. 12፥39። መፍቀሬ ምልክት ወድንቅ ወተአምራት ከመሆን እግዚአብሔር ይጠብቀን።

እግዚአብሔር ከስሕተት ትምህርቶችና አስተማሪዎች፥ ከአጋንንታዊ አሠራሮች፥ ከአሳች ትምህርት ዐውሎ ነፋሶች እና ከክፉ ሠራተኞች ይጠብቀን።

አሜን።

*ዘላለም መንግሥቱ*

© 2016 (፪ሺህ፰) *ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት።*

ezralit@gmail.com / (669)-350-5116